# ክፍል ፫



# ምዕራፍ ፴፫

# ሥራ አለ፤ በጀት የለም

## "ከነጠፈች ላም ወተት ፍለጋ የመጡ!"

*ኬዳም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ ቦርድ በወሰነው መሠረት መነሻቸውን ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጽሕፈት ቤት አድርገው ወደ መላ አገሪቱ የመዘርጋት እና የማገልገል ሥራቸውን ጀምረዋል። ጊዜው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት በልዩ ልዩ አቅጣጫዎች ራሱን እያጠናከረ የነበረበት ወቅት ነበር።*

*ከአሥር ዓመታት በፊት ቀደም ብሎ የተጀመረው የልማት ሥራ የመንግስት ለውጥ በመደረጉ የተነሳ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ ተጠናክሯል። በተለይ እንደ የውሃ ልማት፣ የእርዳታ እና መልሶ ማቋቋም ያሉ ክፍሎችም በአገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች የሚያስመሰግን በጎ ሥራ በመሥራት የቤተ ክርስቲያኒቱን ስም በማስጠራት ላይ ናቸው። ከሁሉም በላይ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ቀድሞ ከነበረበት አንድ ቪላ ቤት እና በጥቂት ኮንቴይነሮች የተወሰነ ቢሮ ወደ ባለ ሦስት ፎቅ ህንጻ ባለቤትነት ተዛውሮ ቃለ ሕይወት እንደ አብያተ ክርስቲያናት ኅብረት ያሉትን ተቋማት የምታስጠጋ ትልቅ ቤተ እምነት አድርጓታል። ጽሕፈት ቤቱ በሕንጻ ብቻም ሳይወሰን በልዩ ልዩ አጋጣሚዎች ከመጡ አጋሮች በተገኘ ድጋፍ የበርካታ የገጠር እና የከተማ መገልገያ መኪናዎች ባለቤትም ሆኗል።*

*በዚሁ ጊዜ ነበር ኬዳም የዋና ጽ/ቤቱ ባልደረባ ሆነው የተቀላቀሉት። የሚሰጡት አገልግሎት "የተንቀሳቃሽ ወንጌላውያን አገልግሎት ክፍል" በሚል ስያሜ በመንፈሳዊ ዘርፍ ውስጥ ካሉት አገልግሎቶች አንዱ ተብሎ ተይዟል።*

*ወንጌላዊውም ይህንን በአገር አቀፍ የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ቢሮ ደረጃ የተዋቀረ ክፍል የማደራጀት እና አገልግሎቱን የማስጀመር ሥራ ያከናውኑ ጀመር። አሁን የጀመሩት አገልግሎት አስቀድመው በጌዶ የወንጌል አገልጋይ በነበሩበት ጊዜም ሲሰጡ የነበረውን በልዩ ልዩ ስፍራ የሚገኙ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናትን የማስተማር አገልግሎት*

በተጠናከረ መልኩ እንዲቀጥል ማድረግ ነበር። ቤተ ክርስቲያናት በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቀኖና እና አወቃቀር ላይ የተመሠረተ መልክ እንዲኖራቸው መምከር እና አገልጋዮችን ማሰልጠን ጀምረዋል።

ይህንኑ አገልግሎት እየሰጡ ለአንድ ዓመት ያህል ከቆዩ በኋላም አገልግሎቱን የማጠናከር እርምጃ ተወስዶ አቶ አዱኛ በዳዳ ከወንጌላዊው ጋር አብረው ለማገልገል ጽሕፈት ቤቱን ተቀላቅለዋል። በዚሁ ጊዜም እነዚሁ አገልጋዮች የመጡበት መንገድ እንግዳ የሆነባቸው እና አስፈላጊነታቸው ጥያቄ የፈጠረባቸው ሁለት የዋና ጽሕፈት ቤቱ ባልደረቦች ቅሬታቸውን ገለጹ። "ሁለት ያለ በጀት ተቀጥረው ሥራ የጀመሩ አገልጋዮች አሉ። ፈጣን ውሳኔ መሰጠት አለበት።" በሚልም በ1989 ዓ.ም አንድ ረቡዕ ማለዳ በዚሁ ጉዳይ ላይ ለመምከር የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች በሙሉ ተሰበሰቡ። ጉዳዩም ዋና ጽሕፈት ቤቱ ከነበረው የገንዘብ አቅም አንጻር አስጊ ስለነበረ "ያለ በጀት የገቡ ሰዎች አሉና ምን መደረግ አለበት?" በሚል ለውይይት ቀረበ። ኬዳም ወደ ዋና ጽህፈት ቤቱ እንዲመጡ ሲነገራቸው በስሙት መሠረት የእነርሱን መምጣት የወሰነው ቦርድ ለካስ ከየትኛው በጀት ለአገልግሎቱ የሥራ ማስኬጃም ሆነ ለሠራተኞች ደመወዝ እንደሚከፈል ያሳለፈው ውሳኔ አልነበረም። ያን ጊዜ በተለያዩ አቅጣጫዎች በማደግ ላይ ያለው ዋና ጽሕፈት ቤት የገንዘብ እጥረት ነበረበት።

ይህንኑ ጉዳይ ለማስረዳትም አንድ የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሠራተኛ ተነስቶ እንዲህ ብሎ ተረተ። "አንድ ጊዜ እኛ አገር አንድ አባት ላም ሊያልብ ዕቃ ይዞ ወደ በረት ገባ። ነገር ግን ወተት አጥቶ ተመልሶ ወጣ። ከዚያም ጥጆች ወደ ላሞቹ ተለቀቁ። በዚህ ጊዜ ልጅየው አባቱ ፈልጎ ያጣውን የቀረ ቢኖር ብሎ ለማለብ ወደ በረቱ ገባ። አባትየው ዋናውን አጥቷል። ልጅየው ጥጃ ከተለቀቀ በኋላ የተረፈ አገኛለሁ ብሎ ነበር የገባው። እናም እኛ እዚህ ኖረን ምንም ባጣንበት ሁኔታ አዲሶቹ እንደ ሰውየው ልጅ የቀረ ፍለጋ ገብተዋል።" ብሎ አዲስ ስለተቀጠሩት ወንጌላውያን ተናገረ።

በዚህ ጊዜ ለዓመት ያህል በአገሪቱ እየተዘዋወሩ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ያለችበትን ሁኔታ ያዩት ወንጌላዊ ኬዳም ለመናገር እድል እንዲሰጣቸው እጃቸውን በማንሳት እንዲህ ብለው መልስ ሰጡ። "አዎ እውነት ነው፤ እናንተ ከላሚቱ ወተት ፈልጋችሁ አጥታችኋል። ለላም ሣር ሳይሰጥ ወተት የለም። እናንተም ለላሚቱ ሣር ሳትሰጡ ከላሚቱ ወተት ፈልጋችሁ አጥታችኋል።" አሉ። ቀጠሉናም "እኔ በቴሌቪዥን የኢትዮጵያን ረኃብ የሚያሳይ ፊልም አይቻለሁ። በፊልሙ እናትየው በረኃብ ሞታ ልጁ የእናቱን መሞት ሳያውቅ ደረቅ ጡቷን ይጠባ ነበር። እናንተም የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መሞቷን ሳታውቁ ዝም ብላችሁ ትጠባላችሁ። እናንተ የምትፈልጉት ገንዘብ ነው።" አሉ እምባ እየተናነቃቸው። በዚሁ ጊዜ ተሰብሳቢው በሙሉ አብሮ ማልቀስ ጀመረና ጸጥታ ሰፈነ። ኬዳም ከቆይታ በኋላ ንግግራቸውን በመቀጠል "ለእኛ ይህ አገልግሎት ከእግዚአብሔር በተቀበልነው ራእይ የተጀመረ ነው። እኛ ወተት ፈልገን አልመጣንም። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሕይወት ይኑራት።

*ከሞት ተነሳ። ... ሲዳማ ውስጥ አንድ መቶ አጥቢያ ወደ ሌላ ቤተ ዕምነት መሄዱን ሰምታችኋል። መቶ ሰው እኮ አይደለም አንድ መቶ አጥቢያ ነው። ይህ እኮ ጉድ ነው። ታውቃላችሁ? እነዚህ ሁሉ ወደ ሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን እና ወደ ሌሎች ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ሄደዋል። ታዲያ ቃለ ሕይወት በሕይወት አለች ማለት ይቻላል?"*

*ይህቺ ላም ሣር አላገኘችም። እንኳን ወተት ልትሰጥ ራሷም ሞታለች። እናንተ ወተት ትፈልጋላችሁ። እኛ ወተት አንፈልግም። በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያኒቱ እራሷ ህያው ትሁን።" በማለት ንግግራቸውን ቋጭተው ስብሰባውም በዚሁ ተዘጋ።*

......................//....................

## በጀት ሳይኖር ማገልገል

ወደ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ለመምጣት እኔ የእግዚአብሔርን ድምፅ የሰማሁት በ1981 ዓ.ም ነበር። ጌታ **"ቃለ ሕይወት ሞተች"** ካለኝ ጊዜ ጀምሮ ብዙ ምልክቶች በማየቴ ጌጃ አጥቢያ ከነበርኩበት ዘመን ጀምሮ የራሴን እርምጃ ለመራመድ ሞክሬአለሁ። በመጨረሻም የቤተ ክርስቲያኒቱ ብሔራዊ ቦርድ በራሱ ጊዜ በ1987 ዓ.ም ቃለ ሕይወትን የማዳን ሥራ ለመሥራት ብሔራዊ ወንጌላውያን በመላ አገሪቱ እየዞሩ አገልጋዮችን እንዲያስለጥኑና ቤተ ክርስቲያናትን እንዲያነቃቁ ወሰነ። ከ1988 ዓ.ም ጀምሮ በዋና ጽሕፈት ቤቱ ሥራ ጀምሬ ተዟዙሬ እንዳየሁትም ቃለ ሕይወት እግዚአብሔር እንደተናገረው የእውነት ሞታ ነበር። የሞተችውን ቤተ ክርስቲያን ከሞት አስነስቶ ህያው ለማድረግም ዋና ሥራዋ የሆነውን በየቦታው የወንጌል ሥራ መሥራት አማኞችን ከዘልማድ የቤተ ክርስቲያን አባልነት ወደ እውነተኛ የክርስቶስ ደቀ መዝሙርነት መቀየር የግድ እንደሆነ አይቻለሁ።

የቤተ ክርስቲያን አባላት ጌታን ፈልገው ተሰብስበው የሚመራ የሚያስተምር አጥተው ትምሕርት አለ ወደተባለበት ሁሉ ግር ብለው ሲሄዱ አይቻለሁ። በሲዳማ ብዙ ሺህ ምዕመናን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያን የጸሎት ቤት ሕንጻ እና ሌላ ሃብት እንደያዙ ጥርግርግ ብለው ወደ ሌላ ቤተ እምነት ሄደው በዓይኔ እያየሁ እንዴት ዝም ማለት ይቻላል?! በእርግጥ በዚያ ወቅት በየቦታው ቤተ ክርስቲያን የነበረችበት በጣም የወረደ መንፈሳዊ አቋም እና የተዘበራረቀ አሠራር ራሱ የሚታይ ቢሆንም የሲዳማ 100 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አንድ ላይ መሄድ ግን የቤተ ክርስቲያኒቱን እውነተኛ ሞት የሚያሳይ ጥሩ ዋቢ ነበር።

ስለሆነም የሥራ በጀት በሌለው ቢሮ ከፍተኛ ሥራ ስላለ ብቻ ለመቆየት ተገደድኩ። እኔ ወደ ቃለ ሕይወት ዋና ጽሕፈት ቤት እንድመጣ ስጠየቅ ጌጃም ልትለቀኝ ከወሰነች

በኋላ ወደ ጽሕፈት ቤቱ ስመጣ ምን እንደምሠራ ዕቅዴን በዝርዝር ጽፌ አስገብቻለሁ። "ባቀረብኩት የሥራ ዝርዝር መሠረት እንዳገለግል ብትፈቅዱልኝ እመጣለሁ። በዚህ መሠረት እንዳገለግል የማትፈቅዱ ከሆነ ግን አልመጣም" በማለቴ ያቀረብኩትን ጥያቄ አይተው "እንስማማለን" ብለው ስለተቀበሉኝ አገልግሎት የጀመርኩት እነርሱ በፈቀዱት እና በተስማሙት መሠረት ነበር።

በዕቅዱ መሠረትም ዋናው ዓላማችን በየቦታው ቤተ ክርስቲያናት ኮንፍረንስ እንዲያዘጋጁ እና በኮንፍረንሶቹ ላይም አገልጋዮችን በመጥራት ስጦታ እንዳላቸው ያረጋገጥነውን ለብቻ መልምለን ስልጠና መስጠት ከዚያም የሰለጠኑትን በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ማሰማራት ነበር። ይህንን ያቀድኩበት ምክንያት ከዚህ ቀደም እንደተረክሁላችሁ በመላ አገሪቱ ለአገልግሎት ስዞር እንደተረዳሁት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚመሩት በግብርና፣ በንግድ እና በሌላ ሥራ በተሰማሩ ሽማግሌዎች ስለ ነበር ነው።

እነዚህ ሽማግሌዎች በትርፍ ጊዜአቸው ቤተ ክርስቲያንን ይመሩ የነበረ ሲሆን በየቤተ ክርስቲያኑ መጽሐፍ ቅዱስ የተማረ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ አልነበረም። "የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ቀጠሩ" ሲባሉም "እኛ የት ሄደን ነው?፤ ምን እንሆናለን?፤ ምንስ እናገለግላለን?" ይሉ ስለነበር ቃለ ሕይወት ውስጧ ተበዝብዞ እያለቀችና እየወደቀች ነበር።

በእቅዳችን መሠረት የኔ ዋና ሥራዬ አገልጋዮችን አሰልጥኖ በየቦታው ማሰማራት ነበር። በዚህ መሠረት በ82 ቦታዎች እንደ ጣቢያ አድርገን ይዘን እየዞርን አገልጋዮችን ማስተማር፣ ተተኪዎችን ማሰልጠን እና ኮንፍረንስ አዘጋጅቶ ሕዝቡን መስበክ ነበር ሊካሄድ የተወሰነው። በ1988 እና 1989 ዓ.ም ለብቻዬ በነበርኩበት ጊዜም ኮንፍረንስ እየተዘጋጀ በየኮንፍረንሶቹ ላይ ማገልገል እና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች በየቤተ ክርስቲያኑ የሙሉ ጊዜ የቃሉ መምህር አገልጋይ እንደሚያስፈልግ ስንሰብክ ነበር የቆየነው። ይህም ቀጥሎ ለምንጀምረው ሥልጠና የሚሆኑ ሠልጣኞች እንድናገኝ የሚያግዝ አካሄድ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ በብዙ ትግል እያገለገልኩ እያለሁ በእኔ ላይ አዱኛ በዳዳ፣ ዮሐንስ ባሰና እና ኤልያስ ጉተላ ተጨምረው ብሔራዊ ወንጌላውያን አራት ሆንን። በወቅቱ ጽሕፈት ቤቱ ደመወዛችንን ከሌላው ሠራተኛ ጋር አብሮ አዘጋጅቶ ስለሚከፍለን የደመወዝ ችግር አልበረብንም። በመጀመሪያ አገልግሎቱን ስንጀምር በትራንስፖርት መኪና እንገለገል የነበረ ቢሆንም በኋላ ግን መኪና ተመድቦልናል። ሆኖም እኛ ወደ ተሰማራንበት የአገልግሎት መስክ ልንወጣ አቅደን ስንነሳ ለእኛም ሆነ ለመኪና የሚሆን ምንም ለመንገድ የሚሆን የወጪ ገንዘብ እንደሌለ ከአስተዳደር እና ፋይናንስ ክፍል ባልደረቦቻችን ይነገረን ነበር።

በዚህ መልኩ ስንጉላላ የቆየነው አራት አገልጋዮች በየነበርንበት ቦታ ጥሩ ተቀባይነት ያለን አገልግሎቱ ጠርቶን የመጣን ሰዎች ነበርን። በብዙ ጫና እየተጨናነቅን ከ1989 ዓ.ም ከመስከረም እስከ ጥር ድረስ ቆይተን አራታችንም በጥር ወር ስለ አገልግሎታችን አካሄድ ወሳይታ ላይ ስብሰባ አደረግን። በዚያ ወቅት ኤልያስ 450.00 ብር፣ ዮሐንስ 700.00 ብር፣ አቶ አዱኛ 700.00 ብር ወርሃዊ ደመወዝ ይከፈላቸው ነበር። እኔ ግን ጌጃ ትከፍለኝ የነበረው ደመወዝ ከፍተኛ ስለነበርና የቡድኑም መሪ ስለነበርኩ ደመወዜ 1100.00 ብር ነበር። "ምንም እንኳ አራታችን ደመወዝ እየተከፈለን የነበረ ቢሆንም ለሥራው የሚሆን የመንቀሳቀሻና ሥራ ማስኬጃ ገንዘብ አልነበረንምና፣ "ምን ይሻለናል?" ተባብለን በጉዳዩ ላይ ጊዜ ወስደን እየጸለይን ብዙ ምክክር አደረግን። በመጨረሻም እግዚአብሔር ድፍረት እና ኃይል ሰጠንና አራታችንም "በረኃብ እንሞታለን እንጂ ይህን አገልግሎት አንለቅም!" ብለን ተስማማን።

በስምምነታችን መሠረት አራታችንም ደመወዛችንን ብቻ እየተጠቀምን እየዞርን ማገልገላችንን ቀጠልን። እኔ ከሚከፈለኝ ደመወዝ ላይ 10 ብር እንኳን ለቤት ሳልሰጥ ጭራሽ ከባለቤቴ ጋር ተማክረን እርሷ ከላሞች ከምታገኘው ገቢ ላይ 300 ብር እየጨመረችልኝ አገልግሎቴን ቀጠልኩ። አጋሮቼ አቶ አዱኛ፣ ዮሐንስና ኤልያስ የየራሳቸውን ደመወዝ ለግል ጉዳያቸው ምንም ሳያስቀሩ ለአገልግሎት ጉዞ እያዋሉ ያገለግሉ ነበር። በዚህ መልኩ አገልግሎት ቀጥለን ግንቦት ወር ላይ ሶላሞ የሚባል አገር እያገለገልን እያለ በድንገት ኤልያስ በኃይል ታመመብን።

እኛም እርሱን ሶላሞ ያለ እንግዳ ማረፊያ (አልቤርጎ) ውስጥ በተያዘለት ክፍል አስተኝተን ወደየ አገልግሎት ምድብ ስፍራችን ተሰማራን። አንድ ቀን እኔ ከማስተምርበት ቦታ መጣሁ እና የህመሙን አይነት እየጠየቅሁ አጫውተው ጀመር። እርሱም የበሽታውን አይነት እና እንዴት እንደሚያደርገው ሲነግረኝ "ይህ እኮ ከምግብ እጥረት እና ከችግር የሚመጣ በሽታ ነው።" ስለው እርሱም "አዎ" አለኝ። ከዚያም "ጋሼ ኬዳሞ ቢያምኑም ባያምኑም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ከማገኛት 400 ብር ላይ አንድ ብር እንኳን ለቤተሰቤ ልኬ አላውቅም።" ሲለኝ ሁለታችንም በሁኔታው በጣም አዝነን እዚያው ጸለይን።

## የበጀት ያለህ!!

ከዚህ ሁኔታ በኋላ እግዚአብሔር ለእኔ ትልቅ እምነት እና ድፍረት ሰጠኝ። ወደ አዲስ አበባ እንደተመለስንም ወደ ዋና ጽሕፈት ቤት መጣሁ እና ሁል ጊዜ "ለጉዞአችሁ በጀት የለም" የሚለን የዋና ጽሕፈት ቤቱ አስተዳደር እና ፋይናንስ ኃላፊ ጋ በመግባት "እኛ ለአገልግሎት ልንወጣ የመንቀሳቀሻ ገንዘብ በጠየቅን ቁጥር 'በጀት የላችሁም' ትላለህ። እናንተ በ1988 ዓ.ም በጀት መዝጊያ ሰኔ ሠላሳ ላይ ለዚህ ዓመት ምን ያህል በጀት ሊያዝ እንደሚገባ፣ ከየት ሊገኝ እንደሚችል፣ መቼ እንደሚመጣ የያዛችሁት እቅድ ነበረ ወይ?" አልኩት። እርሱም "ምንም የተያዘ እቅድ የለም።" አለኝ። እኔም

ወዲያው "ታዲያ አንተስ ይህንን ካልሠራህ ምን ሠርተህ ነው ደመወዝ የምትበላው? ላንተ እዚህ ቁጭ ላልክበት የደመወዝ በጀት ኖሮ ለእኛ የማይኖርበት ምክንያቱ ምንድነው?" ብዬ አፋጠጥኩት። ቀጥዬም "ቁጭ ብሎ በጀት የለም ለማለትማ ለምን ዲግሪ ያለው ሰው ማስቀመጥ ያስፈልጋል? ማንም ቢቀመጥ እኮ በጀት የለም ማለት ይችላል።" አልኩት። ይህን ስናገር እዚያው እኔ ባለሁበት ፊቱ ላብ በላብ ሆነ። እኔም ከእርሱ ጋ ወጥቼ ወደ ዋና ጸሓፊዎቼ ገባሁ። ለአቶ ደምሴና ለዶ/ር ሙላቱም ተመሳሳይ ሃሳብ ነገርኳቸው። ይሁንና እነርሱም መፍትሔ ለመስጠት አስቀድመው ያዘጋጁት ምንም እቅድ ስላልነበረ ለኔ ምንም መልስ ሊሰጡኝ አልቻሉም ነበር።

ዶ/ር ሙላቱ መፍትሔ ቢሆን ብለው "በ1988 ዓ.ም ነሓሴ ወር ላይ በተደረገው የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ከእያንዳንዱ የቃለ ሕይወት አጥቢያ ሃምሳ ሃምሳ ብር በየዓመቱ እንዲሰበሰብ ተወስኖ ቃልም ተገብቶ ነበር።" አሉኝ። እኔም "ታዲያ ይህ ገንዘብ እንዲሰበሰብ ምን መርኃ ግብር አወጣችሁ?" አልኳቸው። እርሳቸውም "በቃ እናንተ ሆራችሁ እንድትሰበስቡ እናድርግ።" አሉኝ። እኔ ግን "ይህ ቢታሰብ እንኳን መታሰብ የነበረበት በመስከረም ወር ላይ ነበር። አሁን ጊዜው ግንቦት ላይ ነን። በዚያ ላይ እኔ ራሴ የምጠቀምበትን ገንዘብ ለመሰብሰብ መቼም አልሄድም።" ብዬ ተቃወምኩ። በዚህ ጊዜ ዮሐንስ "እኛ እንሄዳለን።" ብሎ ሃሳብ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም እኔ ተቆጥቼው ሃሳቡን በመቃወሜ ነገሩ በዚሁ ተዘጋ።

የዚህ ሙግታችን እና ጥያቄአችን ሪፖርትም 'እነርሱ እንዲህ ጠየቁ፤' ተብሎ በአሉታዊ መልኩ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ቀረበ። ሥራ አስፈጻሚውም ጉዳዩን ለብሔራዊ ቦርዱ አቀረበውና ቦርዱ ከኛ አገልግሎት ጋር ቢተያያዝ ዘጠኝ ያህል ጥያቄዎችን አንስቶ እኛ መልስ እንድንሰጥበት አቀረበልን። እኛም በጽሑፍ እንድንመልስ በተጠየቅነው መሠረት በሚገባ አስበንበትና ተማክረን ለዘጠኙም ጥያቄዎች በደንብ የተብራራ ምላሽ ጽፈን ሰጠን።

ከዘጠኙ ጥያቄዎች አንዱም "ችግራችሁ ምንድን ነው?" የሚል ነበር። እኔም በጽሑፍና በተጨማሪም ወደ ቦርዱ ቀርቤ በቃል ሳስረዳ "የኛ ችግር የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሥራ አስፈጻሚዎች ብቻ ናቸው።" ብዬ መለስኩ። ቦርዱም በዚህ ነገር በጣም አዘነ፤ አንዳንዶቹም ችግራችንን ሲሰሙ አለቀሱ። ወዲያውኑም ውሳኔ ተሰጠና "ለዚህ አገልግሎት ሥራ ማስኬጃ የሚሆን 100,000 (አንድ መቶ ሺህ ብር) በአፋጣኝ ከአስተዳደርም ሆነ ከልማት ዘርፍ (ከየትኛውም ገንዘብ ካለው አካል) ተፈልጎ እንዲሰጥ" ተብሎ መመሪያ ተላለፈ።

ከዚህ የተነሳም 1990 ዓ.ም ሲገባ እኛ ያለ ምንም ችግር በነጻነት አገልግሎታችንን አካሄድን። በጀት የለም ሳንባል በዕቅዳችን መሠረት ቃለ ሕይወትን የመታደግ የትንሳኤ አገልግሎት በደስታ እያገለገልን ዓመቱን አገባደድን። በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለንም አንድ ጊዜ የኤስ. አይ. ኤም ዋና ዳይሬክተር ከአሜሪካ መጥተው ዋና ጽሕፈት ቤቱን ጎበኙ። የዋና ጽሕፈት ቤቱ የሥራ ኃላፊዎችም እኛን ጠርተው በአስተርጓሚ አማካኝነት "ምን

እየሠራን እንዳለ፣ የምንሠራበትን ዓላማ፣ እቅድ እና የሥራ አፈጻጸማችንን እንድናቀርብ እድል ሰጡን። ወዲያውኑም ዘጠና ሺህ የአሜሪካ ዶላር ለኛ አገልግሎት የሥራ ማስኬጃ የገንዘብ ድጋፍ ከኤስ. አይ. ኤም ተሰጠ። ያም ገንዘብ እኔ ዋና ጽሕፈት ቤቱን እስከምለቅ ድረስ አላለቀም ነበር። እግዚአብሔር በጀት የሌለውን አገልግሎት ባለ በጀት አደረገው።

………………//……………

# ምዕራፍ ፴፩

# ኢትዮጵያን በቁመቷም በወርዷም መድረስ

## ዘመቻ ትንሳዔ

*ወንጌላዊ ኬዳሞ እና አጋሮቻቸው "የበጀት ችግር ቢኖርም እየተራብን እናገለግላለን" ብለው በመላ አገሪቱ የሚገኙ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናትን የመድረስ አገልግሎታቸውን ተያይዘውታል። ኬዳሞም በውስጣቸው የሚጮኸውን ለዓመታት የቆየ "ቃለ ሕይወት ሞተች" የሚል ድምጽ እያሰቡ ለቃለ ሕይወት ትንሳኤ በመላ አገሪቱ በመዘርጋትና ችግር ሲያጋጥም ደግሞ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ መልስ ይቀበላሉ። አንዳንድ ጊዜም እግዚአብሔር በሰጣቸው ሞገስ እና ጥበብ ፊት ለፊት ተጋፍጠው ያስፈታሉ።*

*አገልግሎቱ በመላ አገሪቱ ከሰሜን ጫፍ (ትግራይ) እስከ ደቡብ ጫፍ (ሙርሲ)፣ ከምስራቅ ጫፍ (ጂግጂጋ) እስከ ምዕራብ ጫፍ (ጋምቤላ) ድረስ የሚዘረጋ በየዓመቱ ሁሉን ስፍራዎች መድረስ አድካሚ እና ትጋት የሚጠይቅ ነበር። ነገር ግን ወንጌላዊው እና አጋሮቻቸው "ለቤተ ክርስቲያን ትንሳኤ የማምጣት ዘመቻ" ብለው የሰየሙትን አገልግሎት በርትተው ለመፈጸም በፍጹም መሰጠት ይሯሯጣሉ። በአገልግሎት ቡድኑ ውስጥ ያሉ አገልጋዮች በአጠቃላይ በአስፈሪው የደርግ ዘመን በጽናት የወንጌሉን ሰንደቅ ከፍ አድርገው ያውለበለቡ እና ብዙ ዋጋ የከፈሉ ነበሩ። መጋቢ ዮሐንስ ባሳና በወላይታ ከባህላዊ ዝማሬ ጀምረው በብዙ ዋጋ መክፈል አልፈው እስከ ታላቅ የወንጌል አገልጋይነት የደረሱ ናቸው። ወ/ዊ ኤልያስ ጉተላም ከቡርጂ ተነስተው በጌዴኦ፣ በሲዳማ እና በሌሎችም አጎራባች ሕዝቦች መካከል ወንጌልን የዘሩ ስለ ወንጌል ዋጋ የከፈሉ ታላቅ አገልጋይ ናቸው። አቶ አዱኛ በዳዳም በነበሩበት የመንግስት የሥራ ኃላፊነት ሳይገደቡ ወንጌላዊ ኬዳሞ ጌጃ አጥቢያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ካገኟቸው ቆፍጣና የወንጌል አማኝ እና ከጌጃ መሪዎች አንዱ የነበሩ የእምነት ሰው ናቸው።*

*ኬዳሞ ከእነዚህ ባለ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ጸጋ ባለቤቶች ጋር በመሆን ነበር በብሔራዊ ወንጌላዊነት ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ትንሳኤ በሀገረ ኢትዮጵያ ስፋት እና ቁመት ላይ የተዘረጉት።*

*በዚሁ አገልግሎት መርሃ ግብር መሠረት የብሔራዊ ወንጌላውያን ቡድን ወደ ምሥራቅ አምርቶ በሐረር እና አካባቢዋ ደጋግሞ ተጉዞ ነበር። በዚሁ ጊዜ ወንጌላዊ ኬዳሞ ምድባቸው አለማያ (የዛሬው ሐሮማያ) ሆኖ በአካባቢው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ስለሌለች በሰው ቤት ውስጥ ያስተምሩ ነበር። በያኔው አለማያ ዩኒቨርሲቲ መምህር የነበረ ዶ/ር ሰለሞን የሚባል ትጉህ ክርስቲያን ቤቱን ፈቅዶ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የነበሩ ጥቂት አማኞች በየምሽቱ የኬዳሞን ትምህርት ሲማሩ ቆዩ።*

*በዚሁ ትምህርት ማገባደጃ ላይም ወንጌላዊው ትምህርቱን ሲከታተሉ ለነበሩ 27 ያህል ሰዎች ከግቢ ውጪ ቤት ተከራይተው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲተክሉ መከሩ።*

*ስለዚህም የተማሩት አማኞች አገልጋይ ሆነው ቦታ ተከራይተው አንዲት የቃለ ሕይወት አጥቢያ ተተከለች። በብሔራዊ ወንጌላውያን የአገልግሎት መርሃ ግብር መሠረትም ከሥልጠና በኋላ በአለማያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አዘጋጅነት በአለማያ ከተማ ኮንፍራንስ ተዘጋጀ። ኬዳሞም ለኮንፍራንሱ ታዳሚ የደህንነት መልእክት አቀረቡ።*

*በኋላም በትንሿ አለምማያ ከተማ በነበረ የመንግስት ትምህርት ቤት በተዘጋጀ ኮንፍራንስ ላይ ብዙ ሰዎች ወንጌል ሰምተው 27 ያህል ወጣቶችም ጌታን አምነው ዳኑ። ዛሬ ያቺ አዲስ አጥቢያ አድጋ ሌላ አዲስ አጥቢያ መትከል ችላለች። ኬዳሞ ዛሬ ያ የብሔራዊ ወንጌላውያን አገልግሎት በመላ አገሪቱ የሰጠውን ፍሬያማ አገልግሎት ሲያስታውሱ ያ ሂደት አሁን ቆሞ በሌላ ዓይነት አሠራር መተካቱ ልክ ነበር ወይ? የሚል ጥያቄ ወደ አዕምሮአቸው ይመጣል።*

......................//...................

## ሥልጠና በ82 ማዕከላት

እግዚአብሔር ለአገልግሎት ሲጠራ የጠራውን ሰው በፍጹም ትቶ አይሄድም። እኔን ለአገልግሎት ጠርቶኝ ካሰማራኝ በኋላም እንዲሁ የእርሱን ታማኝነት አይቻለሁ። እኛ በዋና ጽሕፈት ቤቱ ብሔራዊ ወንጌላውያን ሆነን ማገልገል ስንጀምር በጀት የላችሁም ተብለን ነበር። ነገር ግን የጠራን ጌታ ታማኝ ስለሆነ የለም የተባለው በጀት ተገኝቶ የኛ አገልግሎት የሚያስፈልገው ገንዘብ እና የመጓጓዣ አቅርቦት የተሟላለት ክፍል ለመሆን በቅቷል።

በዚህ አገልግሎት ውስጥ የነበርነው አራት አገልጋዮችም አገልግሎቱን ውጤታማ ለማድረግ አስቀድመን ለብቻ ከከተማ እንወጣ እና በስፋት ተወያይተንና ጸልየን ዓመታዊ እቅዳችንን እናዘጋጅ ነበር። ዓመቱን ሙሉ መቼና የት እንደምንሄድ በደንብ አድርገን እናቅዳለን።

በነበረን የአገልግሎት አጠቃላይ እቅድ መሠረትም በአንድ ወር ውስጥ አራት ጊዜ እየወጣን በአንድ ዓመት ውስጥወደ 82 ጣቢያዎች መድረስ እና ማገልገል ነበር

ፕሮግራማችን። ይህ የኛ ፕሮግራምም በቅድሚያ ወደ ምንሄድባቸው ቦታዎች ሁሉ ይላክ እና ሁሉም በፕሮግራሙ መሠረት ተዘጋጅተው ይጠብቁን ነበር።

ይህንኑ ዝግጅት ለማስፈጸም የአራታችን ረዳት ሆነው በየስፍራው የሚያስተምሩትንም አስቀድመን ወደ ዋና ጽሕፈት ቤቱ እንጠራለን። በዚህም መሠረት ከየጣቢያው የመጡትን እና በየጣቢያው የኛ ረዳት የሚሆኑትን ሁለት ሁለት አገልጋዮች ለሰባት ቀናት እናስተምር ነበር።

ወደየ ጣቢያዎቹ በምንሄድበት ጊዜም አራታችንም ወደ አራት ቦታዎች ተከፋፍለን በመሄድ ሥልጠና ስንሰጥ የምንቆይ ሲሆን በየጣቢያው እንደ ረዳት ሆነው አብረውን የሚሰማሩ ወገኖችም ነበሩ።

ይህንን የሥልጠና መርኃ ግብር ከዘረጋን በኋላ "ሠልጣኞቹ ምን ያህል ዓመት ሠልጥነው ይመረቁ?" የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ነበረበት። የእኛ ቡድን በወቅቱ በቤተ ክርስቲያኒቱ ከነበረው ክፍተት የተነሳ በየሁለት ዓመቱ የሠለጠኑትን እያስመረቅን ሌሎችን ደግሞ ለማሠልጠን ነበር ያቀድነው። ነገር ግን የእኛን አገልግሎት በሚያስተባብሩት የአስተዳደር ኃላፊዎች ለአምስት ዓመት ይሁን ስላሉ በዚያው ተወሰነ። በእርግጥ ይህ ለእኛ በተለይ ሥራውን ለምናከናውነው ከአገልግሎቱ በጥራት መካሄድም ሆነ ከሠልጣኞች በተገቢ ሁኔታ አብሮ መቆየት አንጻር አስቸጋሪ መሆኑን በግልጽ ብናውቅም ውሳኔው የመሪዎቻችን ትእዛዝ ስለነበር ተቀብለን ሥራ ላይ ለማዋል ተገደናል።

በዚሁ ጊዜ ይህ የአምስት ዓመት እቅድ የአገልግሎት ሂደቱን በማጓተት ትልቅ እንቅፋት ፈጠረብን። የመጀመሪያው ችግር በጊዜው በቤተ ክርስቲያናችን ደንብ መሠረት አንድ ሽማግሌ የሚኖረው የአገልግሎት ዘመን አራት ዓመታት ስለነበር ለአራት ዓመታት ካገለገለ በኋላ በድጋሚ ካልተመረጠ ከአገልግሎት ይሰናበታል። ይህም ማለት ለአራት ዓመታት ስናስተምረው የነበረ ሰው ትምህርቱን አጠናቅቆ ሊያገለግል ይቅርና ትምህርቱንም ሳያጠናቅቅ ይሰናበታል። ሌላው አስቸጋሪ ሁኔታ በየጣቢያው የምናስተምራቸው አገልጋዮች ከመብዛታቸውም በላይ በየዓመቱ አዳዲስ ተማሪዎች በየጊዜው የመጨመራቸው ጉዳይ ነው። እኛ ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ ስናስተምራቸው የነበሩትን እንመዘግብ ነበር። በ1991 የጀመሩ፣ በ1992 የጀመሩ፣ በ1993 የጀመሩ ተጨማምረው ትምህርቱ ሳይጠናቀቅ የሠልጣኞች ቁጥር እጅግ እያደገ መምጣቱ ለእኛ ትልቅ ችግር ሆነብን። አንዱ አንድ ዓመት፣ አንዱ ሁለት ዓመት፣ አንዱ ሦስት ዓመት፣ አንዱ አራት ዓመት የተማሩ ብዙ ተማሪዎችም ነበሩን።

ይህንኑ ችግራችንንም አገልግሎቱን በበላይነት ለሚቆጣጠሩት የወቅቱ መሪዎች ማለትም ዶ/ር መኩሪያ ባፋን ለተኩት ዋና ጸሐፊ ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ እና አቶ ደምሴን ለተኩት ም/ዋና ጸሐፊ አቶ ኩርሴ ሸፈኖ አቀረብን። አለቆቻችንም አስቸጋሪ የነበረውን ሁኔታ አይተው ከሦስት ዓመት በላይ የሆናቸውን ሠልጣኞች እንዲፈተኑ እንድናደርግ ነገሩን። እኔም በየዓመቱ መዝግቤ ከያዝኳቸው ተማሪዎች 7 ሺህ ያህል

የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆኑ ሀልጣኞችን በየጣቢያው አስፈትኜ ሥልጠናቸውን አጠናቅቀው ተመረቁ። ከዚያም አዳዲሶችን ጨምረን አገልግሎቱ ቀጠለ።

ይህ በ82 ማዕከላት እየተዘዋወርን የሰጠነው የትምህርትና ሥልጠና አገልግሎት የቃለ ሕይወትን ትንሳኤ ለማምጣት በመላው አገሪቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ የተዘዋወርንበት አገልግሎት ነበር። በብዙ አድካሚና አስቸጋሪ መንገድ ተጉዘን ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከደከመችበት ሁኔታ ወጥታ በእግሯ እንድትቆምና ሥርዓት ያልነበራቸው ቤተ ክርስቲያናት የቤተ ክርስቲያኒቱን ሥርዓት አውቀው እንዲተገብሩ የሚያስችል ሥልጠና ሰጥተናል።

በጊዜው በሰሜን በትግራይ እንኳን በሰባት ቦታዎች ሥልጠና እንሰጥ የነበረ ሲሆን በአንዳንድ ቦታዎች ሰው ጠፍቶ አምስት ተማሪዎች ብቻ በሚገኙበት ጊዜ እንኳን ዋጋ እየከፈልን ሄደን አሰልጥነናል። ከዚያም በጎጃም፤ በጎንደር፤ በወሎ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሚገኙት እንደ ፓዊ ያሉ አካባቢዎች ሳይቀር እየሄድን አገልጋዮችን እናሰለጥን ነበር። በየዓመቱ ይደረግ የነበረው የሰሜን ጉዞአችንንም ለየቦታው በወጣው መርሃ ግብር መሠረት በሰሜን ሸዋ ጀምረን በወሎ አድርገን ትግራይ በመግባት በአክሱምና በሽሬ በኩል አስፈሪውን የሊማሊሞ መንገድ ተጉዘን ጎንደር እና ጎጃም እያልን በአዲስ መንገድ ወደ አዲስ አበባ እንገባለን።

እንደ ሰሜኑ ሁሉ በምዕራብም በኢሉአባቦራ በጋምቤላና በወለጋ እየተዟዟርን የምናሰለጥን ሲሆን በምስራቅም በጂግጂጋ፣ በሐረር እና በድሬዳዋ እንዲሁም በአቅራቢያቸው ሳሉ ከተሞች አገልግሎቱ ይካሄድ ነበር።

ደቡብ ኢትዮጵያ እንደሚታወቀው ጠንካራ የቃለ ሕይወት ይዞታ ስለሆነ እጅግ በርካታ ጣቢያዎች ይገኙበታል። እኛም ከመሀል አገር ከአዲስ አበባ ጀምሮ እስከ ሙርሲ እና ያቤሎ ድረስ ወደ ጠረፍ እየወረድን አገልግለናል። እግዚአብሔር አስቀድሞ ሞተች ያለኝን ቤተ ክርስቲያን ተመልሳ ሕያው እንድትሆን እኔንም ከሠራተኞቹ መካከል የምሆንባትን እድል አግኝቼ አንዱ ተመልሳ ነፍስ ስትዘራ በማየት ወንጌል እንደገና በቤተ ክርስቲያኒቱ አብቦ እንደቀድሞው ብዙ ፍሬ ሲያፈራም ምስክር ሆንኩ።

እኛም በየ አዘቦት ቀኑ ከሰኞ እስከ ሐሙስ ከምናካሂደው ትምህርት እና ሥልጠና ባሻገር በየሳምንቱ መጨረሻ ከአርብ እስከ እሁድ ይካሄዱ በነበሩ ትልልቅ ኮንፍራንሶች ላይ በሰጠነው አገልግሎት ብዙ ሺህ ነፍሳት ሲድኑና እጅግ ብዙ ሺህ ብር ለወንጌል ሥራ ሲሰበሰብ አይተናል።

ከላይ ተነስተው ከነበሩት የሲዳማ ቤተ ክርስቲያናት ጋር በተያያዘም ወደ ሐዋርያት ቤተ እምነት ገብተው ለነበሩት ስለ አስተምህሮተ ሥላሴ ባለ አርባ ገጽ የትምህርት መጽሐፍ አዘጋጅቼ ያንን ትምህርት ተመላልሰን በመሄድ አስተምረናል። ያኔ ሲዳማ ላይ ቤተ ክርስቲያናችን አትመግበንም ብለው ጥለው የኮበለሉ ቤተ ክርስቲያናት ግር ብለው እንደሄዱ ግር ብለው በመመለስ። "በእናታችን ቤትም የሚበላ ተገኝቷል" በማለት መስክረዋል።

እግዚአብሔር እኛን በአብዛኛው የጉልምስና እድሜአችን አልፎ የነበርነውን አገልጋዮቹን ተጠቅሞ አስቀድመን ከሰጠነው አገልግሎት በላይ ቤተ ክርስቲያንን ለማዳን ለታላቅ አገልግሎት ተጠቀመብን። እግዚአብሔር የብዙ ሺህ ቤተ ክርስቲያናት አጀንዳን ለኔ ከገጠር ለመጣሁት ወንጌላዊ አክብሮ ተናግሮ እንደገና ለትልቅ የአገልግሎት ኃላፊነት በማብቃት የከበረ ታላቅ እድል ሰጠኝ።

# ምዕራፍ ፴፫

## እንደገና ወደ ስካንዲኔቪያን /ሰሜን አውሮፓ/

*የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ አገልጋይ የሆኑት ኬዳሞ ወንጌልን ማገልገል ከጀመሩ አምስት አስርት ዓመታት ሊሞላቸው በጣት የሚቆጠሩ ዓመታት ቀርተዋል።*

*በዚህ ወቅት ወንጌላዊው በመላ አገሪቱ እየተዘዋወሩ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንን ከሞት ለመታደግ ዘመቻቸውን በስፋት ቀጥለዋል። እግዚአብሔርም በእርሳቸው እና በቅርብ አብረዋቸው ማገልገል በጀመሩት አጋር ወንጌላውያን እየተጠቀመ ለቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ትንሳኤ መስጠት ጀምሯል።*

*በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበራቸው ስኬታማ አገልግሎት ባሻገርም ኬዳሞ በተደጋጋሚ ወደ ተለያዩ አህጉራት የመጓዝ እና የውጪ ዜጎችን እና በአስከፊው የኮምኒስት መንግስት ስደት በዓለም ዙሪያ የተበተኑ ኢትዮጵያውያንን ማገልገል ችለዋል። በእርግጥ ኬዳሞ በአብዛኛው ወደ ውጪ አገራት የተጓዙት በጊዜ ወንጌላዊ ሆነው እያገለገሉ በነበረበት ጊዜ ነበር።*

*ወደ ዋና ጽሕፈት ቤቱ መጥተው አገር አቀፍ አገልጋይ ከሆኑ በኋላም ወደ ኬንያ ተጉዘው አገልግለዋል። ከቆይታ በኋላም ከዚህ በፊት ወደ ሄዱባት እስካንዲኒቪያን ወደ ተሰኙት የሰሜን አውሮፓ አገራት ሄደው እንዲያገለግሉ ጥሪ መጣላቸው።*

*በጥሪው መሠረት ኬዳሞ ወደ ስዊድን እና ኖርዌይ ሄደው ለማገልገል አቅደው ከአዲስ አበባ ተነሱ። ሆኖም ከዚህ ቀደም የሄዱባት ሌላ የእስካንዲኔቪያን አገር ፊንላንድ የሚገኙ አማኞች ወንጌላዊው በድጋሚ እንዲሄዱ እና እንዲያገለግሉአቸው ስለፈለጉ በሦስቱ አገራት ተዘዋውረው ለማገልገል በቅተዋል።*

*ኬዳሞ ከአገር ከወጡ በኋላ በመጀመሪያ ወደ ስዊድን ነበር የተጓዙት። ስዊድን በነበራቸው የአገልግሎት ቆይታም ከመጋቢ በቀለ ወልደኪዳን ጋር በመሆን ከመላ እስካንዲኔቪያን የተሰባሰቡትን ኢትዮጵያውያን የወንጌል አማኞች ሲያስተምሩ ሰነበቱ። የቆይታ ጊዜአቸውን በጥሩ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ኖርዌይ አመሩ።*

ኬዳሞ ከጥቂት ዓመታት በፊት ወደ እነዚህ አገራት በሄዱበት ወቅት የነበረው የአየር ሁኔታ በአገራቸው ፈጽሞ ታይቶ የማይታወቅ እና እርሳቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ በአሜሪካ ምድር ያዩት ጥጥ የመሰለ የበረዶ ዝናም የሚወርድበት እና እንደ ጦር የሚወጋ አንጀት የሚያንሰፈስፍ ውርጭ ቢሆንም በአሁኑ ጉዞአቸው ግን የገጠማቸው ተቃራኒው ነበር።

ወንጌላዊ ኬዳሞን ወደ ኖርዌይ በመጀመሪያ ጋብዛው የወሰደቻቸው አስቀድመው ያገለገሏት አንዲት አነስተኛ አባላት ያሏት የኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን ነበረች። ይህቺ ትንሽ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ምህረት የምትባል ተጋባዥ እንግዶችን የምታስተናግድ እና በልዩ ልዩ አገልግሎቶች የምትሳተፍ አንዲት አገልጋይ ነበረቻት። ኬዳሞ ወደ ኖርዌይ ባመሩበት ጊዜም ማረፊያ የተዘጋጀላቸው በዚህች የመጨረሻ ልጃቸው ሞክሼ በሆነች ምህረት በተባለች እህት ቤት ነበር።

ምህረት እና ባለቤቷ ኬዳሞን አውሮፕላን ማረፊያ ድረስ በመሄድ ተቀብለው በሚገባ በማስተናገድ በጥሩ ሁኔታ በተዘጋጀ የመኝታ ክፍል እና አልጋ ላይ እንዲያርፉ አደረጓቸው። ኬዳሞም በተደረገላቸው መልካም መስተንግዶ ደስ ተሰኝተው ኖርዌይ ለሚኖራቸው አገልግሎት መዘጋጀት ጀመሩ።

ኖርዌይ በገቡባት በዚያች ምሽትም ምህረት እና ባለቤቷ ያዘጋጁትን ጥሩ እራት ከተመገቡ በኋላ በጉዞ የደከመ አካላቸውን ለማሳረፍ በቶሎ ወደ ምቹው መኝታቸው አመሩ። ሌሊቱን አገባድደውም በ11:00 ሰዓት ነቁ። ወንጌላዊው ከእንቅልፍ ሲነቁ ክፍሉ በኃይለኛ ሙቀት ተሞልቷል። ከነበረው ከፍ ያለ ሙቀት የተነሳ ምንም የሚተነፍሱት አየር ባለማግኘታቸውም ተነስተው የመኝታ ቤቱን በር ከፈቱ። ከክፍሉ ወጥተውም ወደ ሳሎን አመሩ። ሆኖም በሳሎን ውስጥም የሚተነፍሱት አየር ሊያገኙ አልቻሉም። የሌሊቱ ቅዝቃዜ ወይም የንጋት አየር ይኖራል በሚል ተስፋም የሳሎኑን በር ከፍተው ወደ ደጅ ወጡ።

በሚገርም ሁኔታ ግን የውጪው ሙቀት ከውስጡ የባሰ ነበር። ወንጌላዊውም ከሙቀቱ ከፍተኛነት የተነሳ የሚተነፍሱት አየር አጥተው ኃይለኛ የሚያስጨንቅ ስሜት ይሰማቸው ጀመር። በዚህ ከሌሊቱ 11:00 ሰዓት በነበረው ኃይለኛ እና አንዳንድ ጊዜ እስከ 40 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የሚደርስ ሙቀት ውስጥ እንዴት መቆየት እንደሚችሉ ግራ ገብቷቸው ወደ መኝታቸው ተመለሱ።

በመኝታ ክፍላቸው ውስጥ ተንበርክከውም ሁል ጊዜ ለጥያቄአቸው ሁሉ መልስ ወዳለው አምላካቸው መጸለይ ጀመሩ። "እግዚአብሔር ሆይ አታይም ወይ? እኔ ምን እስክሆን ትጠብቃለህ? ያለሁበትን ሁኔታ አታይም ወይ?" እያሉም ጸለዩ። ያ አስጨናቂ ሙቀት እንዳለም ንጋት መጣ፤ ኬዳሞም በነበረው የአየር እጥረት እየተሰቃዩ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ሆነ። በድንገትም ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ኃይለኛ

*ዝናብ መጣል በመጀመሩ ወዲያው የነበረው ሙቀት ቀነሰ። ይህ ዝናብ ኬዳም ኖርዌይ የነበራቸውን የ15 ቀናት ቆይታ እስኪያጠናቅቁ ድረስም እንደቀጠለ ቆየ።*

*በእርግጥ በሰሜናዊው የምድራችን ነፍቀ ክበብ ድንገተኛ የሙቀት ማዕበል በተደጋጋሚ የሚያጋጥም ክስተት መሆኑን በሰሜን አውሮፓ የኖሩ ሰዎች የሚያስተውሉት እና የሚናገሩት ጉዳይ ቢሆንም። የኢትዮጵያን የተመጣጠነ አየር እና ወቅቱን እየጠበቀ የሚለዋወጥ የአየር ጸባይ ተለይተው ለሄዱት ወንጌላዊ ነፍሳቸውን ያስጨነቀው ሙቀት በድንገተኛ ዘናብ መወገዱ ዝናቡም ለቀናት መቆየቱ በትክክል የጸሎታቸው መልስ እንደሆነ በማመን አስደናቂው የእግዚአብሔር ጥበቃ ምን ያህል ከእርሳቸው ጋር እንዳለ እርግጠኛ ሆነው የሚመሰክሩበት አጋጣሚ ሆነላቸው።*

---------------------------//---------------------------------

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ዋና ጽሕፈት ቤት እያለሁ በ1989 ዓ.ም ክረምት ላይ ነበር ወደ ስዊድን የሄድኩት በስዊድን እና አጠቃላይ በእስካንዴኒቪያን አገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዓመታዊ ኮንፍራንስ ይካሄድ ስለነበረ ነው። የዚህ ዓመታዊ ኮንፍረንስ አዘጋጆች እኔ በሄድኩበት ዓመት ከእኔ ጋር የሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነውን መጋቢ በቀለ ወልደኪዳንንም ጋብዘው ስለነበር ሁለታችንም ስዊድን አብረን አገልግለናል።

ይህ ስዊድን ዊተንበርግ የምትባል ከተማ የተዘጋጀ ኮንፍረንስ ለ15 ቀናት ያህል የቆየ ሲሆን፤ ብዙ ኢትዮጵያውያን እና ኤርትራውያን አማኞች ተሰባስበው ተገኝተውበታል። እኔ እና መጋቢ በቀለም በመቀባበል እና እርስ በርስ በመተጋገዝ ጥሩ የአገልግሎት ጊዜ አሳለፍን።

ለአስራ አምስት ቀናት በስዊድን የነበረኝን ቆይታ ካገባደድኩ በኋላም ወደ ኖርዌይ እንድሄድ ተጋብዤ ስለነበር ኖርዌይ የመግቢያ ፈቃድ ለማግኘት ወደሚመለከተው ቢሮ መሄድ ነበረብኝ። አንድ ቀን በአገልግሎት መኃል እረፍት በሆንኩበት ጊዜ እኔን ወደ ስዊድን ጋብዘው ፕሮግራሞቹን ከሚያስተባብሩ አገልጋዮች ከአንዱ ጋር በመሆን ወደ መንግስት ቢሮ ሄድን። ወደ መንግስት ቢሮ ሄጀ ፈቃድ መጠየቅ እንዳለብኝ ሳማክራቸውም ፈቃድን እንድጠይቅ ቢያነስ ግን ለ15 ቀናት ያህል ጠብቄ ፈቃዱን እንደማገኝ ነበር ኢትዮጵያውያኑ የነገሩኝ ስዊድን ውስጥ ፈቃዱ እስኪሰጠኝ ያለ ሥራ ለ15 ቀናት መቆየቱን እያሰብኩ ሄጀ አመለከትኩ። ሆኖም ጥያቄዬ በ15 ቀናት መፈጸሙ ቀርቶ አስፈላጊውን ሰነድ ባቀረብኩ በአስራ አምስት ደቂቃ ጊዜ ውስጥ አልቆልኝ ፈቃዴን ተቀብዬ በደስታ አገልግሎት ወደምሰጥበት ቦታ ተመለስን። በዚህ ፍጥነት ፈቃድ ማግኘቴን የሰሙት የስዊድን አገልጋዮችም በጣም ተደነቁ።

እኔም ወዲያውኑ ወደ ኖርዌይ ሄጄ ለማገልገል ተነሳሁ። ኖርዌይ ስደርስም የጋበዙኝ ምህረት የምትባል የአገልጋይ ልጅ እና ባለቤቷ ከአውሮፕላን ማረፊያ ተቀብለው በጥሩ ሁኔታ ተንከባክበው በራሳቸው ቤት አቆዩኝ።

በኖርዌይ እነ ምህረት የነበሩበት እና ዋናው ጋባዦቼ ሆነው የተቀበሉኝ ቤተ ክርስቲያን አርባ ያህል የሚሆኑ አማኞች የተሰባሰቡባት አነስተኛ የአምልኮ ኅብረት ነበረች። እኔም ለ15 ቀናት ያህል ጊዜ ወስጄ እነርሱን በደንብ ሳስተምር ቆየሁ። ከቀናት በኋላም በዚያው ያለ ወደ 150 ያህል አባላትን የያዘ ትልቅ አጥቢያ ስለነበረ እዚያም ተጋብዤ ሄጄ አስተምሬያለሁ። በጊዜው ትልቁን ቤተ ክርስቲያን ሳይ ሁሉም ነገር የተሟላለት ሆኖ ብዙ ሰውም ያለበት ቢሆንም መንፈሳዊ መነቃቃታቸው ያነሰ ሆኖ ነበር ያገኘሁት። ስለሆነም ሁሉንም ነገር በመንፈስ ቅዱስ ተደግፎ ማድረግ እንደሚገባና ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት ቤተ ክርስቲያን ምንም ማድረግ እንደማትችል ሳስተምራቸው በተሰበረ መንፈስ እያለቀሱ ነበር መልእክቱን የተቀበሉት።

በኖርዌይ የነበረኝን የ15 ቀናት ቆይታ ሳጠናቅቅም እኔ የምሄድበት ሰዓት እነ ምህረት ሥራ ላይ ከሚሆኑበት ሰዓት ጋር ስለተገጣጠመ መሸኘት አልቻሉም። ስለዚህም እኔን አውሮፕላን ማረፊያ የሚያደርስ ታክሲ ጠርቼ እንድሄድ ገንዘብ እና የታክሲ ስልክ ቁጥር ሰጡኝ።

በቤተ ክርስቲያን ሳስተምር የነበረውን ትምህርት ሳጠናቅቅም መዝጊያ ላይ ድንገት የሚሸኝኝ ፈቃደኛ ሰው ካለ ብዬ "እኔን ወደ አውሮፕላን ማረፊያ የሚያደርስ ማነው?" ብዬ ጠየቅኋቸው። አንድ ሰው 'እኔ እሸኝዎታለሁ' አለኝ። እኔ እርሱ ፈቃደኛ መሆኑን ሲነግረኝ እንዲሁ እንደማይሸኝኝ ተሰማኝ። መልሼም "እንዴት እንደሆነ አላውቅም፤ አንተ የምትሸኝኝ አይመስለኝም።" አልኩት። 'እንዴት አልሸኝዎትም? እርስዎ ፈቃደኛ ከሆኑ እሸኝዎታለሁ' አለ። "እኔ ብትሸኝኝ ደስተኛ ነኝ። ነገር ግን አንተ የምትሸኝኝ አይመስለኝም።" "በቃ ነገ በጊዜ መጥቼ እወስድዎታለሁ።" አለ እኔን ለመሸኘት ደስተኛ ሆኖ።

በማግስቱ እኔ ወደ ፊንላንድ ለመሄድ ተነስቼ ዕቃዬን አዘጋጅቼ ሰውየው መጥቶ እንዲወስደኝ መጠበቅ ጀመርኩ። ነገር ግን ሰውዬው የውሃ ሽታ ሆነ። እኔም ሰዓቱ ሲደርስ በጭንቀት መጠበቅ ጀመርኩ። በመጨረሻም ሰዓቱ በጣም በመርፈዱ አውሮፕላን ማረፊያ መድረስ የሚገባኝ ጊዜ አለፈ። ተነስቼ እነ ምህረት በሰጡኝ ስልክ ቁጥር ደውዬ ታክሲውን ልጠራ ስሞክር ቤት ውስጥ ያለው ስልክ አይሠራም ነበርና የባሰ ተጨነቅሁ። በኋላ ቀስ ብዬ በስልኩ ዙሪያ ስመለከት የስልኩ ገመድ ከስልኩ እንደተላቀቀ አይቼ እርሱን አገናኝቼ ደወልኩ እና በተሰባበረ እንግሊዘኛ ከባለ ታክሲው ጋር ተግባብተን መጥቶ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ አደረሰኝ። እኔም አውሮፕላኑ ሊነሳ 10 ደቂቃ ብቻ ሲቀረው ደርሼ ወደ ፊንላንድ በረርኩ።

ፊንላንድ በደረስኩበት ጊዜም ልክ እንደ ኖርዌይ ሁሉ በእነዚህ አገራት ወቅቱ ኃይለኛ ሙቀት ያለበት ስለነበር ተመሳሳይ ነበር። ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር ጮኼ ኖርዌይ መዝነብ የጀመረው ሙቀቱን ያባረረልኝ ዝናብ ፊንላንድም ተከትሎኝ ስለነበር እኔ ፊንላንድን እስክለቅ ድረስ ይዘንብ ነበር።

በፊንላንድም እንዲሁ ለሁለት ሳምንታት ያህል ኢትዮጵያውያን ወንጌላውያን አማኞችን ሳገለግል ቆይቼ በመጨረሻ ወደ አገሬ ለመመለስ ተነሳሁ። ከፊንላንድ ወደ ኔዘርላንድ ሄጄ አምስት ሰዓት ያህል አውሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ቆይቼ ወደ ጀርመን አውሮፕላን ተሳፈርኩ። ከጀርመን በርሬም በመጨረሻ  ወደ አገሬ ገባሁ። በተጠቀሱት አገራት ለሁለት ወራት ያህል አገልግዬ ከተመለስኩ በኋላ በቃለ ሕይወት ይጠብቀኝ የነበረውን ታላቅ አገልግሎቱን ቀጠልኩ።

# ምዕራፍ ፴፮

# የታላቁ አገልግሎት ታላቅ ፈተና

## ባለቤቴ ወ/ሮ ታደለችና ልጇ ሣራ

ወይዘሮ ታደለች ከ 1951 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1991 ዓ.ም ድረስ ለአርባ ዓመታት የወንጌላዊ ኬዳሞ የትዳር እና የአገልግሎት አጋር ሆነው በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አብረው ያለፉ ጠንካራ ሴት ናቸው። ከወንጌላዊው ጋር ገና ለመጋባት ሲወስኑ ኬዳሞ "እኔን ካገባሽ ከአገር አገር ትንከራተቻለሽ. እንጂ ተረጋግተሽ በአንድ ቦታ አትቀመጪም። ወንጌል ለመስበክ በመላ ኢትዮጵያ እንዘዋወራለን።" ብለው አስጠንቅቀዋቸው ነበር። ወንጌላዊው እንደተናገሩትም በተጋቡ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተያይዘው ወደ ዱራሜ በማምራት በጠዛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ግቢ መኖር ነበር እጣ ፈንታቸው።

በዱራሜ ወ/ሮ ታደለች ለኬዳሞ ብቻ ሳይሆን አብረዋቸው ይማሩ ለነበሩ ሁሉ ምግብ እያዘጋጁ ኖረዋል። በዚሁ ጊዜም ከሥራው ባሻገር ነፍስ ጡር ስለነበሩ በግንቦት ወር ለኬዳሞ ሦስተኛ፣ ለራሳቸው በኩር የሆነችውን ልጃቸውን ሣራን ወልደዋል።

ወ/ሮ ታደለች ከዚያ ጊዜ ጀምሮም በሻሾጎ እሽንላ፣ በማረቆ እና በቦቢቾ ከወንጌላዊው ጋር እየተዘዋወሩ በአንድ ቦታ ረግተው ሳይቀመጡ እንደ መጻተኛ ኖረዋል። በሴት አቅማቸውና በወላድ አንጀታቸው ከወንጌላዊው ጋር አገር ለአገር ተጉዘዋል። ከሻሾጎ ማረቆ ድረስ በበቅሎ የበጋ ጸሓይ እየጠበሳቸው ሄደዋል። ማረቆ ሳሉ ባለቤታቸው ለአገልግሎት በሄዱበት ልጃቸው ሃብተወልድን ወልደዋል። በቦቢቾ ማዕከል ከመላው የከምባታና እና ሃዲያ አውራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት የሚመጡ እንግዶችን በጠቅላላ እየተቀበሉ በማስተናገድ ብዙ ለፍተዋል።

አንድ ጊዜ የወ/ሮ ታደለችን በቦቢቾ ብዙ እንግዳ በማስተናገድ መድከም የሚያውቁ እንግዳ በአዲስ አበባ የሚኖሩትን የተባረከ ኑሮ አይተው "አዬ ታደለች በቦቢቾ ያን ሁሉ እንግዳ እያስተናገድሽ፣ ያንን ሁሉ ሰው እየባረክሽ ኖረሽ ዛሬ እግዚአብሔር እንዲህ ሙሉ የሆነ ቤት ሰጠሽ።" ብለዋቸዋል። በጊዜው ወ/ሮ ታደለች አዲስ አበባ ከተማ

ውስጥ በራሳቸው ትልቅ ቤት የሚኖሩና ብዙ የወተት ላሞች ስለነበሯቸው ከራሳቸው አልፈው ለበርካታ ጎረቤቶቻቸው ወተት እየሸጡ በደንብ የተሟላ ኑሮ የሚኖሩበት ወቅት ነበር።

ጌታ ኢየሱስ በስሙ ተጠርተው ስለ ስሙ ያላቸውን የተዉትን ሁሉ በብዙ እጥፍ እንደሚባርክ በሰጠው የተስፋ ቃል መሠረት ወ/ሮ ታደለች እና የወንጌላዊ ኬዳሞ የተቀረው ቤተሰብ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ብዙም ሳይቆዩ የራሳቸውን ቤት ስለገኙ አርፈዋል። ምንም እንኳ ወንጌላዊ ኬዳሞ ከአዲስ አበባ እየተነሱ መላ ኢትዮጵያን ብሎም ዓለምን ቢያዳርሱም የተቀረው ቤተሰብ ግን በአንድ ቦታ ተረጋግተው እየኖሩ ልክ በምሳሌ ምዕራፍ 31 ላይ እንደተጠቀሰችው ሴት ወ/ሮ ታደለች ኑሮአቸውን ቀጥ አድርገው በሥርዓት በመምራት ባለቤታቸው በሰዎች ዘንድ እንዲከበሩ ያደርጉ ነበር። ከብቶች እያረቡ በሚሸጡት ወተት የቤተሰባቸውን ኑሮ ከመደጎም አልፈው የባለቤታቸውን አገልግሎት ሁሉ ደግፈዋል።

ወ/ሮ ታደለችም በተፈጥሯቸው ትጉህ ሴት ስለሆኑ ብዙ ባያርፉም በአዲስ አበባ የነበራቸው ኑሮ ግን ለማረፍ ምቹ ነበር። እኚህ ብርቱ ሴት ወንጌላዊ ኬዳሞ እና ልጆቻቸው ጥሩ ነገር ተመግበው እንዲኖሩ አድርገዋል። ለአገልጋይ ባለቤታቸው ሁሉ ምቹ እንዲሆን በጣም የሚጥሩ ሴት ነበሩ። የሚያስፈልገውን ሁሉ ራሳቸው ገዝተው በማዘጋጀት ቤታቸውን በአግባቡ ይመሩ ነበር። አልፈው ተርፈውም በሰው ፊት የሚቆሙ ባላቸው ሞገስ እንዲያገኙ ከባህላዊ ልብስ አንስቶ የተለያዩ ዘመናዊ አልባሳት ድረስ እየገዙ በስጦታ ያበረክቱላቸው ነበር።

ወንጌላዊ ኬዳሞም ቤተሰቡን በሚመለከት ማንኛውንም ውሳኔ ወ/ሮ ታደለችን ሳያማክሩ እና ይሁንታቸውን ሳያገኙ አይወስኑም ነበር። ከዚህም የተነሳ ሁለቱ ጥንዶች በብዙ መከባበር እና መቀባበል ትዳራቸውን በደስታ በመምራት በርካታ የጸሎት መልሶችን በጋራ ተቀብለዋል።

ወ/ሮ ታደለች በዚህ ሳይወሰኑ ወደ አዲስ አበባ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ እኔ የገጠር ሴት ነኝ ሳይሉ ከከተሜዎቹ ጋር በመግባባት አዲስ አበባ ባለው የጌዴኦ አባላት ኅብረት ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ ያደርጉ ነበር። ከብርቱዎቹ የጌዴኦ እህቶች እና እናቶች ጋር በመሆን እግዚአብሔር በጌዴኦ አጥቢያ የሠራው ታላቅ ታሪክ አካልም ሆነዋል።

ወ/ሮ ታደለች በወንጌላዊ ኬዳሞ ቤት የነበራቸውን ባተሌነት የሚጋራቸውም አላጡም። ግራ በኬዳሞ እና ወ/ሮ ታደለች ቤት ጋብቻው ከተፈጸመ አንድ ዓመት እንኳን ሳይሞላ በ1952 ዓ.ም የተወለደች የቤተሰቡ አባል ናት። ልጅነቷን ጨርሳ እናቷን መርዳት ለመጀመር እና በተከታታይ የተወለዱትን ወንድም እህቶቿን ለመንከባከብ ብዙ ዓመታት አልፈጀባትም። ከሰባት ዓመቷ ጀምራ ለእናቷ ረዳት እና ለታናናሾቿ እንደ እናት ነበረች።

ሣራ በእናቷ ቤት ያሉትን ስድስት ወንድምና እህቶቿን በደንብ ተንከባክባ የምትይዝ ከእነርሱ አልፋ ለወላጆቿም የምትተርፍ መልካም ልጅ ስትሆን በነገር ሁሉ ለቤተሰቧ በጣም አሳቢ ሆና ኖራለች፡፡ ትምህርት እንደጨረሰች በተለያዩ የጤና ተቋማት እየተቀጠረች ሥራ ለመሥራት ሞክራለች፡፡ አንድ ወቅት ላይ በጥርስ ሕክምና ሌላ ጊዜ ደግሞ በዓይን ህክምና ክሊኒኮች ውስጥ በመቀጠር ሠርታለች፡፡ ይሁንና ከዚሁ ሥራ የምታገኘው ገቢ ከእጅ ወደ አፍ ስለሆነባት ከአባቷ ከወንጌላዊ ኬዳሞ 2000 ሺህ ብር ያህል ተበድራ ከገጠር በርበሬ እያስመጣች ሌሎች ቅመማ ቅመሞች ጨምራ እያዘጋጀች ለአዲስ አበባ ነጋዴዎች በማስረከብ ጥሩ ገቢ ማግኘት ጀምራ ነበር፡፡

በዚሁ ጊዜ ሁሉ ሣራ እድሜዋ እየገፋና የትዳር መያዣ ጊዜዋ እያለፈ ቢሄድም እናቷን ጓደኛዋ አድርጋ በሁሉም ነገር የቤተሰቦቿን ቤት መደገፍ ቀዳሚ ሥራዋ ነበር፡፡ በመንፈሳዊ ሕይወቷ አድጋም በዚያ ዘመን ጥሩ አገልግሎት እና ኅብረት በነበረው የጌጃ "ሀ" መዘምራን ኅብረት ውስጥ ታገለግል ነበር፡፡

በዚህ ሁኔታ የኬዳሞ ቤተሰብ ተባርኮ እየኖረ እያለም በ1991 ዓ.ም አንድ ወቅት ላይ እንደተለመደው ወንጌላዊው ዲኒቃ ወደምትባል የከምባታ አካባቢ ቀበሌ በማምራት አገልግሎታቸውን ጀምረው ቀኑን ሲያስተምሩ ውለው ምሽቱን ለማረፍ ወደ ማደሪያቸው ገቡ፡፡ እንደልማዳቸውም በዕኩለ ሌሊት ተነስተው የሌሊት ጸሎታቸውን ከጸለዩ በኋላ ተመልሰው ተኙ፡፡ በዚያ ሌሊትም አንድ ህልም አዩ፡፡

ሕልሙ አጭር ሲሆን ወንጌላዊው፣ ባለቤታቸው ወ/ሮ ታደለች እና ልጃቸው ሣራ ደም የሚመስል ቀለም ያለው ቀይ አፈር ላይ ተቀምጠው ብቻ ነበር ያዩት፡፡ በዚያ በጣም ቀይ ሆኖ በሚታይ አፈር ላይም ሁለቱ ተቀምጠው ያያሉ፡፡ ከሕልማቸው በታላቅ ድንጋጤ ነቅተው ወዲያውኑ "አዬ መሞታቸው ነው!" አሉ፡፡

ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱም ወንጌላዊው በሕልም የአደጋ ምልክት እግዚአብሔር እንዳሳያቸው በማመን ባለቤታቸውን እና ልጃቸውን አነጋገሩ፡፡ ወ/ሮ ታደለችንም "እኔ ለብዙ ሰው አገልጋይ እንደሆንኩ ሁሉ ለእናንተም ወንጌላዊ ነኝ፡፡ እግዚአብሔር ይህንን ህልም አሳይቶኛል፡፡ ስለሆነም ይህ ቀይ አፈር ላይ መቀመጣችሁ የአደጋ ምልክት ነውና ንስኃ የምትገቡበት ነገር ካለ ንስኃ ግቡ፡፡" አሏቸው፡፡

በመጀመሪያ እናት እና ልጅ ወንጌላዊው አደጋ ይጠቁማል ብለው የተናገሩትን ሕልም ለማመን አልቻሉም ነበር፡፡ በኋላ ግን ነገሩ ብዙም ሳይቆይ እውን ሆኖ መታየት ጀመረ፡፡ ወ/ሮ ታደለች በዚያው ዓመት (በ1991 ዓ.ም) ታምመው አልጋ ላይ ሲውሉ የበኩር ልጃቸው ሣራም በ1992 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ታምማ ተኛች፡፡

## ብርቱዋ ታደለች

ታደለች ማለት ለኔ የአርባ ዘጠኝ ዓመታት ዋናዋ የሕይወቱ አካል ነበረች። በተጋባንባቸው የመጀመሪያ ዓመታት ለኔ እና ለእግዚአብሔር ያላትን ፍቅር በሚገባ ያስመሰከረች ብርቱ ሴት ነበረች። ማረቆ እያለን ሁለተኛ ልጇን ኃብተወልድን ስትገላገል እኔ የግድ መሄድ ወደ ነበረብኝ የአገልግሎት ቦታ እንድሄድ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተስማምታ አበረታትታ ልካኝ እርሷ እግዚአብሔር ረድቷት በሠላም ተገላግላ ጠብቃኛለች። እኔ ከሄድኩበት ስመለስም የማረቆ ሴቶች 'እንዴት ብርቱ ሴት ነች' እያሉ በማድነቅ መናገራቸውንና እኔንም በዕልልታ መቀበላቸውን አሁንም ድረስ አስታውሰዋለሁ።

ልክ ገና ድሮ ትዳር ሳልመሰርት በእምባ እንደጸለይኩት ታደለችም እንደ የቀድሞዋ ባለቤቴ ብዙነሽ ሁሉ በጣም እንግዳ ተቀባይ ነበረች። በደረስንበት ቦታ ሁሉ (በተለይ ደግሞ በቢቾ) በነበረን ቆይታ በዝምድና ሰበብም ይሁን እኔ ከየቦታው በአገልግሎት የተነሳ ተዋውቄአቸው ጎትቼ የማመጣቸውን እንግዶች በሙሉ ከልብ ተቀብላ አስተናግዳለች።

ሁለታችን ፍጹም በመከባበር እና በመቀባበል ስለኖርን አንድ ቀን እንኳን ተጣልተን መታረቅ አቅቶን በመካከላችን አስታራቂ አልገባም። የውጪ ሰው ይቅርና የገዛ ልጆቻችን እንኳን እኔና እርሷ መካከል ችግር ሲኖር አያውቁብንም ነበር። አንድ ችግር ሲኖር ሁል ጊዜ ሁለታችን ለብቻችን እስክንሆን በመጠበቅ ወይም ተያይዘን ገብተን የመኝታ ቤታችንን በር በመቆለፍ ልክ እንደ አንድ መንፈሳዊ ስብሰባ በመጀመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ እናነባለን፤ ቀጥሎ ለምንወያይበት ጉዳይ አጀንዳ ይዘን በጉዳዩ ላይ ብቻ እንወያያለን። ፈጽሞ "አንተ እንዲህ ነህ! አንቺ እንዲህ ነሽ!" አንባባልም ነበር።

በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወሰን ውይይት ጀምረን መስማማት ካልቻልን እና አንድ ውሳኔ ላይ ካልደረስን ነገሩ ሳይነካ ባለበት ይቆያል እንጂ በኔ ወይም በእርሷ ውሳኔ ብቻ አይከናወንም። ለምሳሌ አዲስ አበባ ገብተን እኔ 'ጌታ ቤት እና መኪና እንዲሰጠን እንጸልይ' ብዬ ያቀረብኩትን ሃሳብ ሳትቀበል ቆይታ አንድ ምሽት በዝናብ ተደብድቤ ቤት ስገባ አይታ አዝናልኝ እስክትጸጸት ድረስ ለመኪና አልጸለይንም ነበር።

እኔ የጌጃን አጥቢያ ለቅቄ መላ ቃለ ሕይወትን ለማገልገል ሻሾጎ እንኑር ብዬ ያቀረብኩትን ሃሳብም እርሷ "እግዚአብሔር እስኪናገረን አልሄድም።" ብላ ወስና አርፋ ተቀምጣ ነበር። እኔ ለብቻዬ በነገሩ ገፍቼበት ብዙ ዋጋ ከፍዬ እንድተወው እግዚአብሔር አደረገኝ እንጂ።

ከዚህም ሌላ በግቢአችን ውስጥ የሚከራዩ ክፍሎች ለመሥራት እኔ እና ልጃችን ኃብተ ወልድ ሦስት ጊዜ ያህል ምን ዓይነት ቤት እንደምንሠራ የቤት ፕላን ሠርተን ተነስተን ነበር። ነገር ግን ታደለች በሃሳቡ ስላልተስማማች ሳንፈጽመው ቀየን። እኔ ብንሠራ

ትክክል እንደሆነ ባምንበትም እርሷ እስክትስማማ ድረስ ምንም ማድረግ አልችልም ነበር።

እኔ እንደዚሁ የእርሷን ስምምነት ጠብቁ እንደማደርገው ታደለችም ምንም ነገር ከማድረጓ በፊት የእኔን ስምምነት ትጠብቅ ነበር። ይህ የኔ ሃሳብ ካልተፈጸመ ብላ ፈጽሞ ሌላ እርምጃ አትወስድም። በምናደርገው ነገር ሁሉ ከነገሩ በላይ ዋናው ጉዳይ የእኔ እና የእርሷ የልብ አንድነት መሆኑን ሁለታችንም በደንብ ተረድተን ነበር። ከዚህ የተነሳም ምንም ዓይነት ኃይለኛ የሚመስል ችግር በመካከላችን ቢፈጠር ሌላ ሰውም ሆነ ልጆቻችን እንኳን ሳይሰሙ ሁለታችን ብቻ በእግዚአብሔር ቃል፣ በጸሎት እና በውይይት እንፈታው ነበር።

በዚህ ዓይነት ሁኔታ እየኖርን እያለ ነው ከላይ የተተረከው አጋጣሚ የተፈጠረው። በእርግጥ ይህ ነገር ከመፈጠሩ በፊት እኔ ለችግሩ ምክንያት ሆነ ብዬ የማስበው አንድ ጉዳይ ነበር። ከዚህ ቀደም እንደተረክሁት የጌጃ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች እኔ እና ሽመልስ ወዳጆ ቤተ ክርስቲያን ብትዘጋ እንዳንቸገር ብለው የራሳችንን ገቢ ማግኛ እንድንፈጥር መክረውን ነበር። በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን በሰጠችን አንድ ሺህ ብር ላይ የራሳችንን ጨምረን በግቢአችን ውስጥ ከብቶች እናረባ ነበር። ይህንን የከብት እርባታ ሥራ ሁለታችን ተስማምተን የጀመርነው ቢሆንም እየቆየ ግን ለእኔ ስጋት መሆኑ አልቀረም።

ታደለች በጣም ትጉህ ሴት ስለነበረች ከብቶቹ ከተገዙ በኋላ ሁሉን ነገር ራሷ በትጋት ትከታተል ነበር። የከብቶቹን መኖ መስጠት፣ ማለብ እና ሌላውን ሥራ ሁሉ በራሷ ታከናውናለች። የከብቶቹን እበት ለመጥረግ እና ኩበት ለመጠፍጠፍ ብቻ ሠራተኛ ቀጠረች። እኔም ሥራው እርሷ ላይ በጣም እየበዛ እንደሆነ ስላየሁ እንድትተወው ፈለግሁ። ሁል ጊዜ ሳይነጋ አስራ አንድ ሰዓት ተነስታ ወደ ላሞቿ ትሄድ ስለነበር አንድ ወቅት ላይ ብርድ መትቷት ታመመች። እኔም "የነበሩት ላሞች ይሸጡ እና ሥራው ይቁም ወይም ሙሉ ሥራውን ሠራተኛ ተቀጥሮ ይሥራ" ብዬ ሃሳብ አቀረብኩ። (በዚያ ጊዜ የነበሩትን ላሞች በ27 ሺህ ብር ለማግዛት የተስማሙ ሰዎች ነበሩ።) ታደለች ግን "ሠራተኛም አይቀጠርም፤ ላሞቹም አይሸጡም" ብላ እምቢ አለችኝ። እኔም እርሷን ካላሳመንኩ ምንም ማድረግ ስለማልችል የምታከብራቸውን ዶ/ር ሙላትን ሁሉ ቤት ድረስ ጠርቼ ሥራውን እንድትተው እንዲመክሯት የሙጥኝ አልኳቸው። እርሷ ግን እርሳቸውንም አልሰማችም ነበር።

በመጨረሻ በጣም ተበሳጭቼ "አንቺ የምትሞቺው በእነዚህ ከብቶች የተነሳ ነው።" ብዬ ተስፋ ቆርጬ ተውኳት። የእርሷን ፈቃድ ጥሼ ከብቶቹን ብሸጥባት በሁለታችን መካከል መቃቃር ተፈጥሮ መንፈሳዊ ነገራችን ይጎዳል። ከዚህም ሌላ ያለ ስምምነት ያደረግነው ነገር የእኛንም ሥጋዊ ሕይወት ይጎዳል እና ዝም ብዬ እርሷ የምታደርገውን ማየትና መጸለይ ጀመርኩ።

## የሣራ ሞት

እንደፈራሁትም እግዚአብሔር አስቀድሞ ሊያዘጋጀኝ በሌሊት ያሳየኝን ሕልምን ባየሁበት በ1991 ዓ.ም ነሐሴ ወር ላይ ባለቤቴ ታደለች ከወገቧ በታች ያለው የሰውነቷ ክፍል አልታዘዝ እያላት መሰቃየት ጀመረች። ልጃችን ሣራም ብዙ ሳትቆይ በመስከረም ወር እንደ ሳል አድርጎ የጀመራት ሕመም እየባሰ ሄዶ ያሰቃያት ጀመር። ለእኔ ይህ በጣም አስጨናቂ የአደጋ ጊዜ ቢሆንብኝም እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ ሊመጣ ላለው ነገር አዕምሮዬን አዘጋጅቶት ነበር።

የታደለች ሕመም በመጀመሪያ ለመንቀሳቀስ ያስቸገራት ቢሆንም አጣዳፊ በሽታ ስላልነበር ከዚህ ሕመም ጋር ለብዙ ዓመታት መኖር ችላለች። ሣራ ግን በዚያው በታመመችበት ዓመት በጣም ስለተዳከመች ዋካ በሚባል ስፍራ ለማገልገል የያዝኩትን የአገልግሎት ፕሮግራም ለመሰረዝ ፈልጌ ወደ የወቅቱ አለቃዬ አቶ ደምሴ ማዴ ሄጄ "ሣራን በጣም አሟታል።" ብዬ ፈቃድ ጠየቅሁ። እነርሱ ግን የተያዘ ፕሮግራም መሰረዝ የለበትም ብለው ፈቃድ ስለከለከሉኝ ነገሩ ሃሳብ ሆኖብኝ ነበር። በኋላ ግን ፕሮግራሙን ወደያዙት የዋካ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ስደውል ፕሮግራሙ መሰረዙን ነገሩኝና እግዚአብሔርን አመስግኜ ሆስፒታል ወስጄ አሳክሜአት ተመለስች።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በሚያዝያ ወር እኔ ለሌላ አገልግሎት ወደ ባሌ ጎባ ሄድኩኝ። እዚያ እያለሁም በጣም በመታመሟ ተደወለልኝ። ከባሌ ጎባ መልስም በዱራሜ የሚመረቅ ቤተ ክርስቲያን ስለነበር በዕለቱ መልእክት እንዳቀርብ ፕሮግራም ተይዞልኝ ስለ ነበር ከዚያ እስክመለስ ድረስ ሆስፒታል አስገብታ እንድትጠብቀኝ ለደወለችልኝ ለልጄ ለምህረት ነገርኳት። ምህረትም እንደ እናት ሆና ተንከባክባ ያሳደገቻት ታላቅ እህቷን ሣራን በተራዋ ከእህቷ ሙሉ ጋር ሆና ሆስፒታል አስገብታ እዚያው ሆና መንከባከብ እና ጤናዋን መከታተል ቀጠለች። እኔም ቀንና ሌሊት በስልክ ሁኔታዋን እያጣራሁ ባለሁበት ሆኜም አጥብቄ እየጸለይኩ ቆይቼ በመጨረሻ የዱራሜውንም አገልግሎት አጠናቅቄ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ።

ቤት እንደደረስኩም ወደ ሆስፒታል ፈጥኜ ሄጄ አየኋትና እዚያው ሆስፒታል አልጋ ላይ እንደተኛች ከጸለይኩላት በኋላ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ይህቺ ለራሷ ሳታስብ እኔን እና መላ ቤተሰቧን በመውደድ ብዙ ዋጋ የከፈለች ልጅን በማሰብም ቤት ገብቼም መጸለይ ነበር የፈለግሁት። ነገር ግን በዚያ ሰሞን ለመጸለይ በተንበረከክሁ ቁጥር እርሷ ሞታ ለማስተዛዘን የመጡ እንግዶችን ሳስተናግድ እየታየኝ ከተንበረከኩበት እነሳ ነበር። ከሆስፒታል እንደተመለስኩም ምሽቱን ጸለይኩና ድካም ስለነበረብኝ ተኛሁ። ከዚያም ከሌሊቱ ስባት ሰዓትም እንደልማዴ ተነስቼ መጸለይ ጀመርኩ። ጸሎቱን ጨርሼም በጉዞ የተዳከመ ሰውነቴን ለማሳረፍ እንደገና ጋደም አልኩ። ሆኖም በተኛሁበት በህልሜ በቤታችን ሳሎን እኔ ልጆቻችን እና ባለቤቴ ሁላችንም አንድ ላይ

ባለንበት ኤሌክትሪክ ሲይዘን አየሁ። እኔም 'በኢየሱስ ስም!' እያልኩ እየገለጽኩ ኤሌክትሪኩን ከሁላችንም ላይ ለማስለቀቅ እጥር ነበር። ይህንን ሕልም አይቼም ነቃሁ እና ስለ ህልሙ ማሰብ ጀመርኩ። ለራሴም 'በቃ ውዷ ልጄ ሣራ መሞቷ ነው' እያልኩ በኃዘን ስሜት ተውጬ እተክዝ ነበር።

ልክ ከሌሊቱ አስር ሰዓት ሲሆንም ምህረት ስልክ ደወለችና ገና የስልኩን እጀታ አንስቼ ሳነጋግራት ስል ሌላ ምንም ሳትጨምር "ሆኗል!" አለችኝ። እኔም ከህልሙ ጋር አያይዤ ሳስበው ያ ሁላችንንም የሚይዘው ኤሌክትሪክ ኃዘን እንደሆነ አሰብኩ። ወዲያውኑም በቤት ተኝተው የነበሩትን ልጆቼን በሙሉ ጠርቼ ወደ ሳሎን መጡ። ባለቤቴንም ወደ ሳሎን አመጣኋት እና የእግዚአብሔርን ቃል ከፍቼ ካነበብኩላቸው በኋላ ጸልዬ ስለ ሣራ መናገር ጀመርኩ። ሣራ ለእኛ ቤት እንደ እናት ነበረች፤ ያሳየችን ታላቅ ፍቅርና የሠራችው ውለታ ብዙ ነበረ። ለኔ ከልጅነት አልፋ እንደ እህቴም ነበረች።

ይህቺን የቤተሰባችንን ተወዳጅ ልጅና እህት ማጣት አሳዛኝ አደጋ ነበረ። እኔም ከሕልሜ ጋር አያይዤ እግዚአብሔር ሁላችንንም እንዲያጽናና ደግሜ ጸለይኩ። ከዚያም የእርሷን ማረፍ ነገርኳቸው እና እንደገና ጸለይን። ከዚያም ጌታ ልባችንን ደግፎ አጽናናን። ከዚያ ጊዜ በኋላም ሣራን ምንም ያህል ብወዳትም ኃዘኔ ተመልሶ ወደ እኔ አልመጣም።

ይህ ከሆነ በኋላ እኛ በማለዳ ወደ ሆስፒታል ስንሄድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እና አባላት ተነግሯቸው እነርሱ ወደ እኛ መጡ። የሚካሄደው የቀብር ሥነ ስርዓት ፕሮግራምም ወጣ። የጌጃ አጥቢያ ኅብረት ሰዎችም እነ ዶ/ር ሙላት፣ አቶ ደምሴ፣ አቶ ወልደ አምላክ፣ አቶ ጥላሁን፣ አቶ ሽፈራውና ሌሎችም ሁሉም ተሰባስበው መጡና በመኖሪያ ቤታችን ቅጥር ግቢ ሁለት ድንኳኖች ተተከሉ። አስክሬን ሌላ ቦታ እንዲቀመጥ ተደርጎ ለለቅሶ ለመጣው በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወንጌል ይሰበክ ጀመር። ሽፈራው ፈይሳ፣ ዮሐንስ ባሰና፣ አቶ ጥላሁን ... ተራ በተራ ሰበኩ። የሣራ ጓደኞች የሆኑትና አብራቸው ያገለገለችው የጌጃ ቃለ ሕይወት 'ሀ' መዘምራን ዝማሬ እያቀረቡና ሌሎችም ብዙ ፕሮግራሞች ተካሂደው ለቅሶው ታላቅ የኮንፍረንስ ጊዜ ሆኖ አለፈ። እኛም እግዚአብሔር አጽናንቶን ወደ ቀደመው ሕይወት ተመለስን።

ከልጃችን ሣራ ዕረፍት በኋላ ባለቤቴ ታደለችም ከ1991 መጨረሻ ጀምሮ ራሷን ችላ መሄድ የማትችል ታማሚ ሆነችና ከምናውቃቸው እና ከሚያውቁን ብዙ ዶክተሮች መፍትሄ ለማግኘት ብዙ ጥረት ተደረገ። በመጨረሻም ትድናለች በሚል ተስፋ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ገብታ ቀዶ ጥገና ተሠርቶላት በመጠኑ የተሻላት ቢሆንም ፍጹም ድና ቆማ መሄድ ግን አልቻለችም። በተወሰነ መልኩ ቀስ ብላ ቤት ውስጥ እንድትንቀሳቀስበት ቆማ የምትሄድበት የሚገፋ መደገፊያ ገዛሁላትና በእርሱ ትንሽ ትንሽ ትንቀሳቀስ ነበር። በቤት ውስጥ ሆና ተደግፋው እንድትንቀሳቀስም እኔና ልጃችን ኃብተ ወልድ ረጃጅም ብረቶች አስገብተን እንዲመቻት አድርገን ሠራንላት። ነገር ግን

ባተሌ የነበረችው ሴት ተኝታ ስትውል የሰውነቷ ክብደት እየጨመረ ስለሄደ ከአልጋ ወርዳ መንቀሳቀስ ሁሉ እየከበዳት መጣ።

እንግዲህ በዚህ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ ነበር የቃለ ሕይወትን ትንሳኤ ለማምጣት ከአጋሮቼ ጋር የምንዞረው። በአንድ ዓመት ውስጥ በ82 ጣቢያዎች የሚገኙ በደንብ ተመዝግበው የተያዙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን እየሄድን በማስተማርና ኮንፍረንሶችን በማካሄድ ወንጌልን እንሰብካለን። ያመነትም እውነተኛ ደቀ መዝሙር እንዲሆኑ እና መስቀሉን እንዲሸከሙ እናስተምራለን። እግዚአብሔር ኃይሌ ሆኖም የገጸው ፈተና ቢያይልም የጌታን አገልግሎት አላጓደልኩም ነበር።

---------------------//---------------------

# ምዕራፍ ፴፯

# የብሔራዊ ወንጌላዊነትና ዋናው ጽሕፈት ቤት

## አምስተኛው ብሄራዊ ወንጌላዊ

*የብሔራዊ ወንጌላውያን አገልግሎት በቃለ ሕይወት ውስጥ እንደሚገባ ተጠናክሮ በመሰጠት ላይ ነው። የዚህ አገልግሎት ክፍል ባልደረቦች የሆኑት አራቱ አገልጋዮች በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ግቢ ከሚገኘው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ወይም የጸሎት ቤት ውስጥ ያለች ትንሽ ቢሮ በመነሳት በመላ አገሪቱ ይዘረጋሉ። በቢሮአቸው ደጃፍ ላይ ጽፈው በለጠፉት "እነሆ በእኛ ላይ አለቃ እግዚአብሔር ነው" 2ኛ ዜና 13:12 የሚል ጥቅስ ሃሳብ ላይ በመመርኮዝ አገልግሎቱን የራሳቸው አድርገው በብዙ ዋጋ መክፈል በትጋት ለቤተ ክርስቲያን ተጋድሶ ይማስናሉ። ከእነዚሁ አራት የአገልግሎት ተጣማጆች ጋርም አብሮ ወደ 82ቱም ጫቢያ የሚጓዝ አንድ ተጨማሪ አጋር ነበር።*

*ወንድም ጻድቅ ጸሓይ ከሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተገኘ የብሔራዊ ወንጌላውያን የአገልግሎት ክፍል የሚገለገልበትን ሃርድ ቶፕ ላንድ ክሩዘር ቶዮታ መኪና የሚያሽከረክር ብርቱ ሾፌር ነበር። ጻድቅ ወደ ቃለ ሕይወት ገብቶ ብሔራዊ ወንጌላውያንን ጭኖ በመላ አገሪቱ መዞር ሲጀምር ብቸኛ ወጣት ነበር። በጥቂት ጊዜያት ውስጥም ትዳር ይዞ የልጆች አባት መሆን ቻለ። ይህ በረከትም ለጻድቅ ጭንቀት ፈጠረበት። በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ለብሔራዊ ወንጌላውያኑም ሆነ ለተቀጠሩ ሾፌሮች በአጠቃላይ የሚከፈላቸው ደመወዝ እጅግ አነስተኛ ስለነበር ጻድቅ ከቃለ ሕይወት በሚያገኘት በጣም አነስተኛ የሆነች ደመወዝ ቤተሰቡን ለመምራት በጣም ተቸገረ።*

*የብሔራዊ ወንጌላውያንን ክፍል የሚያስተባብሩት ኤዳሞ በወቅቱ የጻድቅ የቅርብ አለቃ ስለ ነበሩ ከእርሱ ጋር በቅርበት በመነጋገር እና በመመካከር ተከባብረውና ተደማምጠው ይሠሩ ነበር። ከዚህም አልፎ ጻድቅ ባለው እጅግ የተረጋጋ ማንነት እና ታጋሽ ባህርይ የተነሳ በብሔራዊ ወንጌላውያኑም ሆነ በመላው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች የተወደደ ባልደረባ ነበር።*

*አንድ ቀን ኬዳሞ ወደ ቢሮአቸው ሲገቡ በልባቸው ለጻድቅ የሆነ ነገር ማለት እንዳለባቸው እየተሰማቸው ነበር። ወንጌላዊውም ቢሮ እንደደረሱ ሥራ መፍታት የማይወደው ጻድቅ ታጥባ የቆመች መኪናውን እየወለወለ ከሚያጸዳበት ጠርተው ያናግሩት ጀመር። "ጻድቅ ይህን ሥራ ዝም ብዬ እተዋለሁ ብለህ እንዳታስብ በጣም ተጠንቀቅ። ገንዘብ ስለሚያንስህ የተሻለ ወደሚከፍለኝ ልሂድ ብለህ ሥራህን በፍጹም እንዳትለቅ። ምንም ከመወሰንህ በፊት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቅ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካወቅህም ሁሉንም ነገር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አድርግ እንጂ በራስህ አንዳች ነገር እንዳታደርግ። አንተ እኮ ከእኛ ጋር የምታገለግል ከእኛ እኩል የሆንክ አስተማሪ፣ ወንጌላዊ ነህ።" እያሉ ብዙ መከሩት። በዚህ ጊዜ ጻድቅ አንገቱን አቀርቅሮ በማዳመጥ ላይ ሳለ ሰውነቱ ይንቀጠቀጥ ገባ። ከዚያም ለወንጌላዊው ሊያደርግ የወሰነውን እና እየጸለየ የነበረውን ጸሎት ነገራቸው።*

*ጻድቅ በዚያ ዘመን ለሾፌር ትልቅ ሊባል የሚችል 1,600.00 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ) ብር ደመወዝ ሊከፍለው የሚችል ድርጅት አግኝቶ ለመግባት እያሰበ ነበር። ይህ ደመወዝ ደግሞ በቃለ ሕይወት ከሚያገኘው በሁለት እጥፍ አካባቢ የበለጠ እና ቤተሰቡን ትቶ በመላ አገሪቱ የሚያደርገውን መንከራተት የሚቀንስለት ነበር። ነገር ግን ወንጌላዊ ኬዳሞ ሊያደርግ ያሰበውን ምንም ሳያውቁ እንዲያው በመንፈሳቸው ተረድተው የሰጡት ምክር ልቡን ስለነካው ያገኘውን መልካም ዕድልም አሳልፎ ለሌላ ለመስጠት ወሰነ። በብሔራዊ ወንጌላውያን ሹፌርነትም አገልግሎቱን ቀጠለ።*

*ከጥቂት ዓመታት በኋላ ጻድቅ በብሔራዊ ወንጌላውያን ሾፌርነት እያገለገለ በነበረበት የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት አንድ ዜና ተሰማ። ባለቤቱ ምልታ በላከችው የዲቪ ቅጽ አማካኝነት የጻድቅ መላው ቤተሰብ አሜሪካ በክብር ለመኖር የሚያስችለው የዲቪ ሎተሪ እድለኛ አሸናፊ ሆነ። በአጭር ጊዜ ውስጥም እርሱ እና ቤተሰቡ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ሠራተኞችን በፍቅር ተሰናብተው ተጸልዮላቸው ወደ አሜሪካ አመሩ። ዛሬ ጻድቅ ከቤተሰቡ ጋር አሜሪካን አገር መልካም ኑሮ ይኖራል።*

## ጻድቅ እውነትም ጻድቅ /ስምን መልአክ ያወጣዋል/

ጻድቅ የእኛ ክፍል ሾፌር ሆኖ ሲመጣ ለእኛ እንደ ተዓምር ነበር። ምክንያቱም አገልግሎታችን ወደ ብዙ ቦታ መጓዝ የሚበዛበት አድካሚ ሲሆን ከዚህም የተነሳ ሥራው ጥሩ ችሎታ፣ ትዕግስት እና ባህርይ ያለው ሾፌር ይፈልግ ነበር። ሆኖም እንደ አለመታደል ሆኖ የእኛ አገልግሎት በተጀመረባቸው የመጀመሪያዎቹ ሦስት ዓመታት ከእኛ ጋር ይሠራ የነበረው ሾፌር በጣም አስቸጋሪ ነበር።

የእኛ ቡድን አባላትም ሁኔታውን አይተው ወዲያውኑ ነበር ከእርሱ ጋር መሄድን በመጥላት ከእኛ እንዲለይ መጠየቅ የጀመሩት። እኔም "ይህን ሰው እኛ ካልቻልነው ማን ይችለዋል?" ብዬ እነርሱን እየለመንኩ ከእኛ ጋር እንዲቀጥል ለማድረግ ሞከርኩ።

ነገር ግን እርሱ በፍጹም ሊስተካከል የሚችል ዓይነት ሰው አልነበረም። መኪናውን በፍጥነት መንዳት ባለበት ቦታ (በተለይ እኛ ቸኩለን እንዲፈጥን ከፈለግን) እርሱ በአርባ (በሰዓት 40 ኪ.ሜ) ይነዳል። መኪና ሊፈጥን በማይችልበት አደገኛ መንገድ ላይ ስንሆን ደግሞ ከመቶ በላይ (በሰዓት 100 ኪ.ሜ) እያበረረ መኪናውንም እኛንም ያሰቃይ ነበር። በዚያ ላይ ሁል ጊዜ በየደረሰበት በረባ ባልረባው ከመሬት ተነስቶ ከሰው ጋር ይጣላል።

ከዚህ የተነሳ እኔ ይለወጣል በሚል ተስፋ ለበርካታ ጊዜያት እያለቀስኩ ብመክረውም እርሱ ግን የሰው ምክር ለመቀበል ምንም ፍላጎት አልነበረውም። በዚህ ዓይነት እየተሰቃየን ስናገለግል ቆይተንም አንድ የዓመቱ መዝጊያ ላይ የአገልግሎት ግምገማ ለማድረግ እና ለመጪው ዓመት ለማቀድ ቡድናችን ባቦጋያ ላይ ከተመ። በዚሁ የባቦጋያ ቆይታችን ባደረግነው ስብሰባ ላይም ይህ ሾፌር ተነሳ። በኋላ እኔ እንደ ቀድሞው ልናገር ስል ባልደረቦቼ እኔን እየተቀበሉ ተናገሩ። የሾፌሩም ችግር ተዘረዘረ። አነዳዱ ችሎታ ባያንሰውም ከባህርይው አስቸጋሪነት የተነሳ አንድ ቀን እኛ ላይ አደጋ ሊያደርስብን ይችላል። በሄደበት ሁሉ ከሰው ጋር የሚፈጥረው ግጭት ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ለሚኖራት ምስክርነት መልካም አይደለም። "እኛ ሦስት ዓመት ሙሉ ታግሰነዋል፤ እርሱ ግን ምንም ለመለወጥ አይፈልግም።" ተባለ።

በመጨረሻም ያኔ ምክትል ዋና ጸሐፊ ወደ ነበሩት አቶ ደምሴ ማደ ሄጀ "ቢቃ እኛ ከዛሬ ጀምሮ ከዚህ ሾፌር ጋር መሄድ አንችልም። መኪናችሁንም ሾፌራችሁንም ውሰዱ። እኛ እንደ ድሮአችን በአውቶብስ እየዞርን እናገለግላለን።" አልኳቸው።

አቶ ደምሴም ተደናግጠ ሌላ ሾፌር እንደሚመድቡልን ነገሩን። ሾፌሩም ከኛ ክፍል ወደ ሌላ ተዛውሮ መሥራት ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ በዚያ ወቅት የቃለ ሕይወትን የታሪክ መጽሐፍ እያዘጋጀ የነበረው ወንድዬ ዓሊ መረጃ ለማሰባሰብ ሲሄድ እርሱን ይዞ ከሄደበት ሲመለስ መንገድ ላይ መኪናው ተገለበጠ። ሾፌሩ ሞተ፤ ወንድዬ ዓሊ ግን በተዓምር ተረፈ።

ጻድቅ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ካለፍን በኋላ ስለመጣ ነበር በጣም ደስ የተሰኘንበት። እኛጋ ከመጣበት ዕለት ጀምሮም አንድ ቀን እንኳን ሳንጋጭ በፍጹም መከባበር አገልግሎታችንን ማካሄድ ችለናል።

ጻድቅ አዲስ ሾፌር ሆኖ እንደመጣ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሰባት ቤት ጉራጌ ከምክትል ዋና ጸሐፊያችን አቶ ኩርሴ ጋር ነበር የሄድነው። ከኛ ጋር አገልግሎት እንደጀመረም ብዙ ሳንቆይ አንድ ጊዜ ወደ ይርጋ ዓለም እየሄድን አንድ የእኛን ረዳት ይዘን ለመሄድ አዋሳ ውስጥ ብዙ ቦታዎች ስንዳዝ በጣም መሸብን። እናም ማደሪያ ቦታችን ሳንደርስ ከምሽቱ አምስት ሰዓት አለፈ። እኔም የእርሱ ልፋት አሳዝኖኝ "ጻድቅ ተቸገርክ አይደል?" አልኩት። እርሱ የሰጠኝ ምላሽ ግን "እንዴ ጋሼ ሥራ እኮ ነው!" የሚል ነበር።

ጻድቅ በጣም ታጋሽና አስተዋይ ሰው ሲሆን እኛ የጠየቅነውን ሁሉ ይታዘዘን ነበር። ከዚህ የተነሳም ልክ እንደኛ የሆነ አገልጋይ አድርገን ነበር የምንቆጥረው። በእርግጥም አገልግሎታችን ስኬታማ እንዲሆን እርሱም በተሰጠው ችሎታ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ጻድቅ እውነትም ጻድቅ አገልጋያችን ነበር።

## ሴቶች መምራት የለባቸውም!

በቃለ ሕይወት ዋናው ጽሕፈት ቤት በነበረኝ ቆይታ ማብቂያ አካባቢ አንድ ነውጥ ተፈጥሮ ነበር። በዋና ጽሕፈት ቤት የመንፈሳዊውንና የልማት ዘርፉን ሥራዎች የሚያስተባብሩ እና የሚያከናውኑ ብዙ ቢሮዎች ነበሩ። እግዚአብሔር ቃለ ሕይወትን ባርኮ ብዙ ሰዎች በዋና ጽሕፈት ቤቱ ያገለግሉ ነበር። ለእነዚሁ በመቶዎች ለሚቆጠሩ አገልጋዮችም ዘወትር ማለዳ ማለዳ ጸሎት የሚካሄድ ሲሆን በየበዓሉ እና በየወቅቱም የሙሉ ቀን የጸሎት ፕሮግራሞች ሳይቋረጥ ይዘጋጃሉ።

እኔም በዚህ የዋና ጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች የጸሎት ጊዜ ላይ እኛ አዲስ አበባ በምንሆንበት ጊዜ ሁሉ ተገኝቼ እካፈል የነበረ ሲሆን ለብዙ ጊዜያትም እድል እየተሰጠኝ አገለግያለሁ። ይህንኑ የዋና ጽሕፈት ቤቱን የጸሎት ፕሮግራም ስመለከትም ፕሮግራሙን የሚያስተባብሩት በአብዛኛው ሴቶች መሆናቸውን አየሁ። እነዚሁ ሴቶች ብዙ ጊዜያትም የጸሎት ፕሮግራሙን ከማስተባበር አልፈው ይመራሉ። በኔ እይታ የዋና ጽሕፈት ቤት ግቢ ማለት በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ከቃለ ሕይወት ጋር ግንኙነት የሚፈጥሩ አካላት ሁሉ የሚመጡበት ቢሮ ነው። ስለዚህ በዚህ ፕሮግራም ላይ የሴቶች አመራር መስፈኑ ለሚመጡ እንግዶች ምን መልዕክት ያስተላልፋል በሚል ሳስብበት ቆይቼ አንድ ማለዳ በዚሁ ፕሮግራም ላይ እንዳስተምር እድል ስለተሰጠኝ እኔም በዚሁ ጉዳይ ላይ ተዘጋጅቼ መጥቼ በኃይል ተናገርኩ።

የዋና ጽሕፈት ቤቱ ግቢ ሌሎች በትኩረት የሚያዩት ስለሆነ ምሳሌ መሆን እንዳለበት በቃለ ሕይወት አስተምህሮ መሠረት ሴቶች መምራት እንደሌለባቸውና መሪ መሆን እንደማይችሉ አስተማርኩ። ከዚሁ ጋር አያይዤም አለባበስንም በሚመለከት ሴቶች የትም ሲሄዱ የሚለብሱትን ዓይነት እዚህ መልበስ እንደሌለባቸው እና በጣም አጭር ቀሚስና እና ጥብቅ ያለ ሱሪ መልበስ እንደሌለባቸው ከረር አድርጌ ተናገርኩ።

ወዲያው በግቢው ውስጥ ግርግር ተፈጥሮ ብዙዎች ተቆጥተው ወደ ዋና ጸሐፊዎቹ አቶ ኩርሴ እና ዶ/ር ተስፋዬ ቢሮ በመሄድ ቅሬታቸውን ገለጹ። አንዳንዱ ተቃውሞም ለኔ ለራሴም ደረሰኝ። አቶ ኩርሴ እና ዶ/ር ተስፋዬም በጉዳዩ ዙሪያ ጠርተው ያናግሩኛል ብዬ ብጠብቅም ሳይጠይቁኝ ቀሩ። ከተወሰነ ጊዜ በኋላም በዚያ ወቅት የዋና ጽሕፈት ቤቱ ባልደረባ ያልሆነው አቶ ደምሴ መጥቶ ስለ ጉዳዩ አነጋገረኝ። ፕሮግራሙ አነስተኛ እንደሆነ እና እዚያ ላይ ሴቶች ቢመሩ ምንም ችግር እንደሌለበት

ሊያስረዳኝም ሞከረ። እኔም ግቢው ዓለም አቀፋዊ እንግዶች የሚስተናገዱበት የመላ አገሪቱ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት መሪዎች የሚሰባሰቡበት እንደሆነና ፕሮግራሙም ለሌሎቹ ሁሉ አርዓያ መሆን እንዳለበት ነገርኩት።

ነገር ግን ሴቶች ይህንን የጸሎት ፕሮግራም መምራታቸውን የሚደግፉ ወገኖች የእኔን ሃሳብ ሊቀበሉ አልቻሉም። በኋላም ይህንኑ ጉዳይ "መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ወይስ አይደለም?" ብሎ የሚያጠና ኮሚቴ ተቋቋመ። በዚሁ ኮሚቴ ውስጥም ዶ/ር ተስፋዬ እና አቶ ኩርሴ ተካትተው ጥናት ተደረገ።

በመጨረሻም የእኔ ሃሳብ ተቀባይነት አግኝቶ ወንዶች ፕሮግራሙን እንዲያስተባብሩ እና እንዲመሩ ተወሰነ። ይህ መወሰኑን የተቃወሙ አንዳንድ ወገኖች ግን በኔ ቅር ተሰኝተው ቀሩ። እኔም በዋና ጽሕፈት ቤቱ ያለኝ ቆይታ የማብቂያ ጊዜ እንደተቃረበ የሚያሳይ ምልክት አድርጌ ወሰድኩት።

# ምዕራፍ ፴፰

# የቃለ ሕይወት ዋና ጽሕፈት ቤት ቢሮን ለመልቀቅ መወሰን

## የዋና ጽሕፈት ቤቱን የአገልግሎት ድንኳን መንቀል

ኬዳሞ የወንጌሉን ቀሊል ቀንበር ከተሸከሙ ብዙም የቆዩ ሳይመስላቸው አምስት አስርት ዓመታት ያህል ነጉደዋል። እርሳቸውም እንደ ዋዛ የሰባ አምስት ዓመታትን እድሜ አስቆጥረዋል። በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት በብሔራዊ ወንጌላውያን የሚሰጠው አገልግሎትም ውጤታማነቱ ታምኖበት በቂ በጀት፣ ለገጠር መንገድ ምቹ እና ጠንካራ የሆነ መኪና፣ በባህርይም ሆነ በችሎታው ከተዋጣለት ሾፌር ጋር ተመድቦ እንደሚገባ በመከናወን ላይ ነው።

ይሁንና ወንጌላዊ ኬዳሞ በዚህ እድሜአቸው ከአራቱ እድሜ ጠገብ አጋሮቻቸው ጋር በመላ አገሪቱ በመዞር የሚያካሄዱት ሥልጠና በተመሳሳይ መልኩ መቀጠሉ አዳጋች እንደሚሆንና አንድ ቀን እንደሚቆም ታይቷቸዋል። ስለሆነም አገልግሎቱ ስልቱን እንዲቀይር ባልደረቦቻቸውንና አለቆቻቸውን መወትወት ጀምረዋል። ሆኖም አጋሮቻቸውም ሆኑ የሥራ ኃላፊዎቻቸው ጥያቄአቸውን አልተቀበሉትም። በነዚህና ከዚህ ቀደም ከጠቃቀሷቸው ሌሎች ምክንያቶች የተነሳም ወንጌላዊው ከብሔራዊ ወንጌላዊነት ለመሰናበት ወሰኑ። ይህንኑ ውሳኔአቸውን የሚያሳውቅ ደብዳቤም ጥቅምት 27 ቀን 1994 ዓ.ም ለመልቀቅ ከፈለጉባቸው ምክንያቶች ሁለቱን ጠቅሰው ለዋና ጽሕፈት ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች አስገቡ።

በዚህ መልኩ የብሔራዊ ወንጌላዊነት አገልግሎቱን የማቆም ፍላጎታቸውን ለዋና ጽሕፈት ቤቱ ገልጸው ምላሽ በመጠባበቅ ቆዩ። ወንጌላዊው ይህንኑ ውሳኔ ወስነው እና ከብሔራዊ ወንጌላውያኑ የቀደመ አገልግሎት አካሄድ ተለይተው "የወንጌል ተልዕኮ ዓላማ እና አፈጻጸም" የሚል መጽሐፍ አዘጋጅተው እርሱን ለአገልጋዮች እያሰለጠኑ ቆዩ። ከዋና ጽሕፈት ቤቱም ሳይለዩ ምላሽ እየጠበቁ እና በግላቸው እንዴት እያገለገሉ እንደሚቀጥሉ ሳይወስኑ ወራት አለፉ። ምንም ከራሳቸው የዕድሜ ሁኔታ እና በአገልግሎቱም ዙሪያ ካሉ አንዳንድ መሰናክሎች የተነሳ ከዚህ የአገልግሎት ክፍል መለየት እንዳለባቸው ቢረዱም ፍጹም ቆርጠው ለመወሰን ግን ተቸግረው ቆይተዋል።

*አንድ ረቡዕ ማለዳ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት በወር አንድ ጊዜ የሚደረግ የሠራተኞች የግማሽ ቀን የፆም እና የጸሎት ፕሮግራም በመካሄድ ላይ ነበር። ኬዳሞም ይህንኑ ፕሮግራም ለመካፈል በተለመደው የመጀመሪያ ረድፍ ጥግ ላይ ያለች ወንበራቸውን ይዘዋል። ፕሮግራሙ ተጀምሮም በተለያዩ አገር አቀፋዊ የወንጌል ርእሰ ጉዳዮች ላይ ጸሎት ተደርጎ ዝማሬ እና መልዕክት ቀረበ። በዕለቱ መልዕክት እንዲያቀርብ የተጋበዘው እንግዳም የተኃድሶ እንቅስቃሴን ጀምረው ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የወጡት የአማኑኤል ኅብረት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሆነ ወጣት ነበር። ያ ወጣት አገልጋይም የዕለቱን መልእክት በዘፍጥረት ምዕራፍ 13 ላይ ባለው የአብርሃም ታሪክ ላይ መስርቶ አቀረበ።*

*በዚህ ክፍል ውስጥ ባለው ታሪክ ላይ አብርሃም ከሎጥ ከተለየ በኋላ እግዚአብሔር "ተነሣ በምድር በርዝመትዋም በስፋትዋም ሂድ፤ እርስዋን ለአንተ እሰጣለሁና።" ብሎ ከተናገረው በኋላ "አብራምም ድንኳኑን ነቀለ..." ይላል። ዘፍጥረት 13:17-18*

*አገልጋዩ ይህንኑ ክፍል በጉባኤው ከተገኙት የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጽሕፈት ቤት ሠራተኞች ሕይወት ጋር ሲያዛምድም "አብርሃም ድንኳኑን እንደነቀለ በዚህ ጉባኤ መካከል የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የምትጸልዩ አላችሁ። ድንኳናችሁን መንቀል ያቃታችሁ አላችሁ። እግዚአብሔር ከተናገራችሁ በኋላ እንደ አብርሃም በእምነት ድንኳናችሁን ልትነቅሉ እና ልትጓዙ ይገባችኋል።" አለ።*

*ኬዳም ይህንን መልዕክት ሲሰሙ እግዚአብሔር እየተናገራቸው እንዳለ ገባቸው። አገልጋዩ በግልጽ እየሰበከ ያለው ነገር ለእርሳቸው ሕይወት የሚሆን መልእክት ነበርና በዋና ጽሕፈት ቤት ለሰባት ዓመታት የተከሉትን የአገልግሎት ድንኳን ሊነቅሉ ወሰኑ። ወዲያውም መወሰን በመቻላቸው ውስጣቸው በደስታ ሲጥለቀለቅ ተሰማቸው። ያቺን ዕለት እና የመጣውን መልእክትም በአጀንዳቸው ላይ ጽፈው ያዙ። ዕለቱ ረቡዕ ሰኔ 5 ቀን 1995 ዓ.ም ነበር።*

--------------------//------------------

በብሔራዊ ወንጌላውያን አገልግሎት ሥር በመላ አገሪቱ እየተዘዋወርን በቤተ ክርስቲያኒቱ ልዩ ልዩ መዋቅሮች እና በሺዎች በሚቆጠሩት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ የነበረውን ወጥ ያልሆነ እና የተዘበራረቀ መንፈሳዊ አገልግሎት የማቅናት ሥራ ስንሠራ ቆይተናል። ይህንኑ ቤተ ክርስቲያንን የማቅናት አገልግሎት በመስጠት ሂደት በአገሪቱ አራቱም ማዕዘናት ባሉ አጥቢያዎች የሚገኙ ሰባት ሺህ ያህል አገልጋዮችን አሰልጥነን አስመረቅን።

ይህንኑ ሥልጠና በማጠናከርም በሁለተኛ ዙር ሌሎች ብዙ ሺዎችን ማሰልጠን ቀጠልን። ይሁንና ከላይ ገልጬው በነበረው መልኩ በመላ አገሪቱ በሚገኙ 82 ጣቢያዎች በዋና ጽ/ቤቱ ያለነው አራት አገልጋዮች ብቻ በዋነኛነት አሠልጣኝ ሆነን

እየተዘዋወርን ማሰልጠናችን ለኔ አንድ ቀን የሚቆም እንደሆነ እና በዚህ መልኩ ብዙም መዝለቅ እንደማልችል ይታየኝ ጀመር። ስለሆነም እየሰጠን ያለነውን ውጤታማ አገልግሎት ለብዙ ዓመታት ቀጣይ እንዲሆን የሚያደርግ ስልት ማውጣት እንዳለብን ማሰብ እና ለሌሎችም ማካፈል ጀመርኩ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለንም አንድ ቀን በተመሳሳይ መርኃ ግብር ጅማ ሄደን አገልግለን ስንመለስ የአገልግሎት ስልታችንን መቀየር እንዳለብን አንስቼ መወያየት ጀመርን። በዚሁ ጊዜም በመኪናችን ውስጥ ብሔራዊ ወንጌላውያን ከሆንነው ከአራታችን ባሻገር ሹፌራችን ጻድቅ እና አንዳንድ ጊዜ አብሮን ሄዶ ረዳቶቻችን በማይኖሩበት ቦታ የእኛ ረዳት በመሆን እንዲያገለግል እንጋብዘው የነበረው ኢሳይያስ ኤርሳቦም አብሮን ነበር።

በዕለቱ እኔ የአገልግሎት ስልታችንን ስለመቀየር ሳነሳ እንድናደርገው ያሰብኩት የሚከተለውን ስልት ነበር። እኛ እንደ ቀድሞው በዓመት ውስጥ የምናስተምረውን ትምህርት እቅድ አጠቃላይ በመላ አዲስ አበባ መጥተው እኛ ያሰለጠንናቸው እና በተጨማሪ የምናሰለጥናቸው አገልጋዮች በየሚሄዱበት ቦታ ትምህርቱን ያስተምራሉ። እኔ ይህን እቅድ እንድንተገብር ሃሳብ ያቀረብኩበት ምክንያትም እኛ አሁን በመላ አገሪቱ እየዞርን እያገለገልንበት ያለው አድካሚ አካሄድ አንድ ቀን ሊቆም ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ ትምህርቱን ተረክቦ የሚያስቀጥል ማንም ስለማይኖር በአንድ ጊዜ ይቋረጣል። ሰልጣኞቹ በየአገራቸው የሚያስተምሩ ከሆነ ግን እኛ ብናቆምም ይህ ውጤታማ አገልግሎት አይቆምም።

እኔ ይህን ነገር ስናገር በደንብ አስቤበት ስለነበረም እኛ ያዘጋጀነውን ትምህርት የማስተማሪያ መጻሕፍት አንዳችን ብቻ ከሾፌር ጋር በመኪና ሄደን በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ በብዙ ቦታ ማዳረስ እና መመለስ እንችላለን በማለት ለማስረዳት ሞከርኩ። በእስከ አሁኑ አገልግሎት ግን ወደ አንድ ቦታ ብቻ የሚደረግ አንድ ጉዞ ለሳምንት ነበር የምናደርገው።

በዚህ ጊዜ አቶ አዱኛ በዳዳ እና ዮሐንስ ባላና በዚሁ መልኩ መቀጠል አለብን ብለው ተሟገቱ። እኔ ሁኔታውን ሳስረዳቸውም በተወሰነ መልኩ የተቀበሉ መስለው ነበር።

በኋላም ይህንኑ ሃሳብ ይዘን ወደ ዋና ጽሕፈት ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ቀረብን። በዋና ጸሓፊዎች ፊት ስንነጋገርም ዮሐንስ ወደ ቀድሞ አቋሙ ተመልሶ አገልግሎቱ በቀድሞ መልኩ መቀጠል እንዳለበት ተናገረ። የወቅቱ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች የነበሩት እነ ዶ/ር ተስፋዬም አገልግሎቱ በተጀመረው መልኩ እንዲቀጥል እነ ዮሐንስ የያዙትን አቋም ደገፉ። በዚህ ጊዜ እኔ በዚህ መልኩ እየተንገዝኩ እንደማልቀጥል ወሰንኩ።

ይህንኑ ውሳኔዬን ለማጽናትም የአገልግሎት ስልቱ ካልተቀየረ በዚህ መልኩ እየተሂሂርኩ መቀጠልን ያሰሁበት ዕድሜም እንደማይፈቅድ እና በዋና ጽሕፈት ቤቱ

አገልጋይ ሆኜ ለመቀጠል የማልችልበትን ሌላ ሁለተኛ ምክንያት ጠቅሼ ጥቅምት 27/2004 ዓ.ም የመልቀቂያ ደብዳቤ ለዋና ጽሕፈት ቤቱ መሪዎች አስገባሁ።

በእርግጥ ያኔ ደብዳቤዬን ስጽፍም ሆነ በኋላም የዋና ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች በቃል ሲያናግሩኝ ያልጠቀስኩትና ለመልቀቁ ምክንያት የሆነ አንድ ተጨማሪ ዋና ጉዳይም ነበር።

## መጋቢ ዮሐንስ ባሳና

ከእኔ ጋር በብሔራዊ ወንጌላዊነት ከሚያገለግሉት ሦስት አገልጋዮች መካከል ዮሐንስ ባሳና በጊዜው በጣም ትልቅ ስም ያለው ትልቅ አገልጋይ ነበር። እርሱ በጣም ጎበዝ አገልጋይና ልዩ የስብከት ስጦታ የነበረው ሰው ነው። መጋቢ ዮሐንስ የወላይታ ምድር ካፈራቻቸው ታላለቅ የወንጌል አገልጋዮች አንዱ ሲሆን ልክ እንደ እኔ ሁሉ በዋና ጽሕፈት ቤቱ ብሔራዊ ወንጌላዊ ከመሆኑ በፊት በበርካታ የአገልግሎት መስኮች ፍሬያማ አገልግሎት የሰጠ እና ብዙ ዋጋም የከፈለ ነበር። ከእኛ ቡድን ጋር በነበረው አገልግሎትም መደረግ ያለበትን ሁሉ ለማድረግ የሚያስችል ስጦታ ነበረው።

ነገር ግን ዮሐንስ የእኛ አገልግሎት በመላ አገሪቱ በስፋት የሚሰጥ ከመሆኑ የተነሳ በዓመት ውስጥ አብዛኛውን ጊዜያችንን ለዚህ አገልግሎት ለማዋል የሚያስገድደን ሁኔታ ለእርሱ ችግር ሆኖበት ነበር። ከብሔራዊ ወንጌላዊነት አገልግሎት ነጻ ሆነን በየግላችን የአገልግሎት ፕሮግራም ከምንይዝባቸው በወር ውስጥ ያሉ አንድ እና ሁለት ሳምንታት በላይ በርካታ የኮንፍረንስ ስብከት አገልግሎት ግብዣዎች ይመጡለት ነበር።

እርሱም ግብዣዎቹን ተቀብሎ ፕሮግራም ይይዝ ስለነበር እኛ ወደ ተለያዩ ንዑስ ጣቢያዎች ለማሰልጠን እና ለመስበክ ስንሄድ እርሱ ግን ወደ ተጠራበት ኮንፍረንስ ስለሚሄድ የእርሱ የአገልግሎት ምድብ ብዙ ጊዜ ባዶ እየሆነ ተቸግረናል። ይህንን ከአገልግሎታችን ጅማሬ አንስቶ የነበረ ችግር እንዲፈታም ብዙ ጥረናል። በየዓመቱ በምናደርገው ስብሰባ እና የሥራ ግምገማ ሂደት ይህ መስተካከል እንዳለበት በተደጋጋሚ ተነጋገርን። ሆኖም ሌሎቻችን ነጻ በምንሆንበት ሳምንት ብቻ የግል ፕሮግራማችንን ስንወጣ እና ሄደን ስናገለግል እርሱ ዋናውን የእኛን ፕሮግራም ጥርቅም አድርጎ ዘግቶ የራሱን ፕሮግራም ይፈጽማል። በዚህ መልኩ በተደጋጋሚ ጭቅጭቅ እና መወቃቀስ በመካከላችን ተከስቶ ነበር።

አንዳንድ ጊዜም እርሱ አስቀድሞ የተቀበለውን ፕሮግራም በመያዝ በዝምታ ቆይቶ ልክ ሁለት ሳምንት ሲቀረው የጋበዙትን ሰዎች ይዞ ወደ እኔ ይመጣል። እኔም "አይቻልም፤ የራሳችን ፕሮግራም አለን!" ስል ሰዎቹ በእኔ ቅር ይሰኛሉ፤ ብፈቅድ ደግሞ የእኛ ፕሮግራም ይበላሻል። በዚህ መልኩ እኔን አጣብቂኝ ውስጥ እየከተተኝ ለበርካታ ዓመታት ስንቸገር ቆየን። የእርሱን ነገር ጠቅሰን የሥራ ኃላፊዎቻችን ወደ ሆኑት ወደ እነ ዶ/ር ተስፋዬ እንዳናመለክት ደግሞ እኔ እና ዮሐንስ የወንጌል

አስተማሪዎች በመሆናችን ከመንፈሳዊ ብስለት አንጻር እኛ ከእነርሱ በልጠን መታየት አለብን። እነርሱ ያኔ ከእኛ የሚበልጡት በሥልጣን ብቻ ነው። ስለሆነም እኔ እና ዮሐንስ በሥራም ቢሆን ተካስሰን እነርሱ ፊት መቅረብ ለእኔ ሞት መስሎ ነበር የታየኝ። ስለሆነም ለእነርሱ ሳልናገር እኛው ብቻ በየጊዜው እየተወቃቀስን ለሰባት ዓመታት ተጓዝን።

በመጨረሻም አንድ ቀን በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ስንወያይ ዮሐንስ በነገሩ ተሰላችቶ "በቃ እኔ ይህንን አገልግሎት ትቼ ወደ ወላይታ እመለሳለሁ" አለ። ይህ ለኔ በጊዜው በጣም አስደንጋጭ ነበር። በዚያ ዘመን የወላይታ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ከቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽሕፈት ቤት ጋር የተጋጩበት ጉዳይ ስለነበራቸው ከወላይታ የመጣው አገልጋይ ዋና ጽሕፈት ቤቱ አልተስማማኝም ብሎ ወይም አባረረኝ ብሎ ወደ ወላይታ ቢሄድ በነበረው ግጭት ላይ ተጨማሪ ይሆናል። ስለሆነም ዮሐንስ ያቀረበውን ሃሳብ ተቃወምኩ።

"ዮሐንስ አንተ ትጉህ ሰው ነህ። ይህንን ሥራ በኃላፊነት ብትይዘው ጨምረህ ትሠራለህ እንጂ ሰነፍ አይደለህም። በዚያ ላይ አንተ ትልቅ ስጦታ አለህ። ስለሆነም የዚህን አገልግሎት ኃላፊነት አንተ ውሰድ እና ምራ። እኔ ከዳር ሆኜ ለብቻዬ አገልግሎቴን እቀጥላለሁ፤ "በዚህ ላይ እኔ እና አንተ መቼም አንጣላም፤ አንካሰስምም፤ እኛ ተጣልተን እና ተካስሰን አለቆች ጋር ብንቀርብ ለሁለታችንም የሞት ሞት ነው። በማጭድ እንደ መታረድ የከፋ ነው።" ብዬ ጨመርኩ እና አገልግሎቱን ለእርሱ ለማስረከብ ተስማምተን ወሰንን። በመጨረሻም እርሱን አንበርክኬ እጄን ጭኜ ጸልዩለት አገልግሎቱን አስረከብኩት።

ለዋና ጽሕፈት ቤቱ ባስገባሁት የሥራ መልቀቂያም የሁለታችንን ችግር ሳላነሳ ነበር የጻፍኩት። ዮሐንስም አገልግሎቱን ለማስቀጠል ለተወሰነ ጊዜ ሞከረ። ሆኖም ከዋና ጽሕፈት ቤቱ ኃላፊዎች ጋር በደንብ ተግባብቶ ለመቀጠል ባለመቻሉ የዋና ጽሕፈት ቤቱን የአገልግሎት ኃላፊነት ለቅቆ ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ወላይታ ሶዶ ገባ። በዚህ ጊዜ እኔ ነገሩን አይቼ ልክ እንዳልሆነ ባውቅም ዝም ለማለት ሞክሬ ነበር። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ዝም ማለት እንደሌለብኝ ስለወቀሰኝ ተነስቼ ወላይታ ድረስ ሄጄ ዮሐንስን አገኘሁት።

በመጨረሻም "ከዋና ጽሕፈት ቤት አትውጣ። አገልግሎትህንና ጌታ የሰጠህን ስጦታ እንዴት ታስራለህ?" ብዬ አጥብቄ ተማጸንኩት። እርሱም ሊቀበለኝ ስላልቻለ እያዘንኩ ተመለስኩ። ዮሐንስ ባሳና የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው ታላላቅ የወንጌል አገልጋዮች በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት መካከል አንዱ ነው። ራሱን ወደ ኋላ በመመለሱ እና በመላ አገሪቱ የነበረውን አገልግሎት አቁሞ በአንድ ቀጣና ውስጥ ብቻ ለማገልገል መወሰኑ በበኩሌ ዛሬ ነጻነቱን አሳልፎ ሰጥቶ እራሱን እንዳሰረ ሆኖ ነው የታየኝ። ያንን ባያደርግ ኖሮ መጋቢ ዮሐንስ ባሳና ዛሬ ዓለም አቀፋዊ ታላቅ አገልጋይ ይሆን ነበር።

# ምዕራፍ ፴፱

# የብዙዎች አባት / እንደገና ወደ አሜሪካ

## ሡናይት ኬዳሞ

*ምንም እንኳን ዘመኑ እግዚአብሔር የለም የሚባልበትና የእግዚአብሔርን መኖር ማመን የሚያስከንንበት ወቅት ቢሆንም ትንሿ የጌጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ግቢ ግን የታፈረችና የእግዚአብሔር መኖር ከነ አስደናቂ ጥበቃው እና ከግልጽ ምሪቱ ጋር የሚታይባት ቅጥር ነበረች። መላ አገሪቱን የወረረው የሞት፣ የድህነትና የተስፋ ቢስነት በሽታ ጌጃ መሠረተ ሕይወት ግቢ ሲገባ ይቀየራል። የተስፋ፣ የእምነትና የጽናት መንፈስ በግቢው እና በግቢው ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ ይታያል።*

*ከሰኞ እስከ አርብ ሕጻናት እና ታዳጊዎች በመላ አገሪቱ የማርክሲዝም ሌኒንዝም ኃይማኖት የለሽ ርዕዮተ ዓለም ትምህርት ጆሮአቸውን ከሚያደነቁረው አኩዮቻቸው በተቃራኒ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ እና ስሙን እየጠሩ ይማራሉ። በየምሽቱ ከመላው የአዲስ አበባ አብያተ ክርስቲያናት የሚሰባሰቡ አገልጋዮች ለነገ ብቃት እንዲጨምሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ይማራሉ። ቅዳሜ እና እሁድ ከልጅ እስከ አዋቂ ቅዱሱን እግዚአብሔርን ያመልካል፤ ስለ እርሱ ይማራል፤ ለክብሩ ይዘምራል፤ ለአገልግሎትም ይዘጋጃል። በተለይ እሁድ ማለዳ ገና ሰማይና ምድር በደንብ ሳይላቀቅ ጀምሮ እስከ እኩለ ቀን የጌጃ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ የብዙዎች መገለገያ ማዕከል መሆኗን ታስመሰክራለች። ህዝበ እግዚአብሔር ቃሉን ለመስማትና ህያው አምላኩን ለማምለክ እንደ ዳበ እና ስኳር ወረፋ ይሰለፋል።*

*የዚህ ሁሉ አስደናቂ የእግዚአብሔር ሥራ ታሪክ እና አስፈሪ ዘመን አስደሳች ህብረ ዜማ አቀናባሪ እንዲሆኑ ከተጠሩት አገልጋዮች መካከል አንዱ እና ግንባር ቀደሙ ደግሞ ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ነበሩ።*

*አንድ እሁድ ማለዳ ኬዳሞ ግርማ ሞገስ በሆኑለት የጌጃ ግቢ ውስጥ እየተዘዋወሩ ነገሮችን እያስተዋሉ ነው። አማኞች እንደተለመደው ወንበር ለማግኘት እየተጣደፉ ወደ አምልኮ አዳራሹ ይተምማሉ። በዚህ ጊዜ ኬዳሞ ዓይናቸው አንድ ነገር አስተዋለ። አንዲት ወጣት ሰውነቷ ላይ የተጣበቀ ኮት እና ሱሪ ለብሳ መላ የሰውነቷ ቅርጽ*

ቆልጭ ብሎ እየታየ ወደ አዳራሹ ታመራለች። ኬዳሞ ተንደርድረው ወደዚህች ልጅ አመሩ። "የኔ ልጅ እቤትሽ ሌላ ከዚህ የተሻለ ልብስ የለሽም ወይ?" አሏት።

ልጅቷም "አለኝ" ብላ መለሰች።

"መኖሪያ ቤትሽ የት ሰፈር ነው?"

"ጨርቆስ" ብላ መለሰች።

"በቃ ቅርብ ስለሆነ ሂጂ እና ለከኛ ልብስ ቀይረሽ ለብሰሽ ነይ፤ እኔ ቢሮ ሆኜ እጠብቅሻለሁ፤ ወደ ቢሮዬ ነይ" አሏት። ልጅቷም ታማኝ ነበረችና ቤቷ ሄዳ ልብስ ቀይራ በቀጥታ ወደ ኬዳሞ ቢሮ መጣች። ኬዳሞም ጊዜ ወስደው ከመከሯትና ከጸለዩላት በኋላ ባርከው ሸኟት። ከዚያ በኋላ በተደጋጋሚም ወደ ቢሮአቸው እየመጣች በመንፈሳዊ ሕይወቷ እንድታድግ ምክርና ጸሎት ተደርጕላታል። ያቺ ሠናይት ከበደ ትባል የነበረች ልጅ በጌጃ መሠረተ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብዙም አልቆየችም። ከብዙ ዓመታት በኋላ ኬዳሞ ካናዳ ለአገልግሎት በሄዱ ጊዜ ሠናይትን ቶሮንቶ አገኟት።

ሠናይት ኬዳሞን ካናዳ ባገኘቻቸው ጊዜ ደስታዋ ወደር አልነበረውም። ለወ/ዊ ኬዳሞ ሙሉ ልብስ፣ ከረባት፣ ጫማ... አንድም የጎደለ ነገር ሳይኖር ገዝታ በስጦታ አበረከተች። ለኬዳሞ ብቻም ሳይሆን በጊዜው አብረዋቸው ለተጓዙት የወላይታ ምድር ታላቅ የወንጌል አርበኛ ለሆኑት አባባ መርኪና መጃም ከኬዳሞ ጋር አብረው ስለነበሩ ይህንኑ የፍቅር ስጦታ አበረከተች። ሠናይት ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ዛሬም ድረስ ለኬዳሞ አንዳንድ የፍቅር ስጦታ እና ገንዘብ ትልካለች።

ኬዳሞ በባዕድ አገር ከሠናይት ጋር በተገናኙበት ጊዜ አንድ ነገርም አስተዋሉ። ቀድሞ ሠናይት ከበደ ትባል የነበረችው ልጅ አሁን ሠናይት ኬዳሞ ተብላለች። ኬዳሞም ሠናይትን "ለምን?" ብለው ጠየቁ። ሠናይትም "እኔ አባቴም እንደ እርስዎ መክሮኝ፣ ገስጾኝ፣ ተቆጥቶኝ አያውቅም፤ እኔ ዛሬ ሰው የሆንኩት ያኔ እርስዎ በመከሩኝ ምክር ነው። ስለዚህ እኔ ሰናይት ኬዳሞ ተብዬ ልጠራ ይገባል" አለቻቸው።

ኬዳሞ ጌጃ በነበራቸው የአገልግሎት ቆይታ እንደ ሠናይት ሁሉ ብዙዎች ሕይወታቸው ተለውጧል። የማያምኑ አምነዋል፤ ያልበረቱ ወላዋዮች ጸንተዋል፤ የደከሙ በርትተዋል፤ ያልተማሩ ተምረዋል። እግዚአብሔር ለብዙ ሺዎች መነሳት፣ መታነጽና ማደግ ምክንያት አድርጎ ተጠቅሞባቸዋል። እግዚአብሔርም ታማኝ ስለሆነ በየደረሱበት በእርሳቸው አገልግሎት የተባረኩ ልጆቻቸው አስታውሰው እንደገና እርሳቸውን እንዲባርኩ አድርጓቸዋል። ኬዳሞም ብዙ ልጆች የሰጣቸውን አምላካቸውን ሁል ጊዜ ይባርካሉ።

--------------------//--------------------

ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አሜሪካን አገር የሄድኩት እኔ እና ቤተሰቤ ምቹ ባልሆነ ሁኔታ ላይ እያለን ነበር። እኔ ከኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ለመልቀቅ እያሰብኩ ያለሁበት፤ ባለቤቴ ታደለችም ታምማ አልጋ ላይ ከሰነበተች ብትቆይም በዚህ ጊዜ ህመሟ ጸንቶባት ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ወንዱ ልጄ ኃብተ ወልድም እንዲሁ ታምሞ የኔን ክትትል እና ድጋፍ የሚፈልግ ሲሆን ይባስ ብሎም ትንሿ ልጄ ምህረት የመጀመሪያ ልጇን ልትወልድ ተቃርባለች። እኔም በዚህ ሁሉ ሁኔታ ውስጥ እያለሁ የአሜሪካን የአገልግሎት ጥሪ መጣ።

እኔ ወደ አሜሪካን እንድሄድ የቀረበልኝ ጥሪ የመጣውም አስቀድሞ እግዚአብሔር ራሱ ወደ አሜሪካ እንደምሄድ ከተናገረኝ በኋላ ነበር። አንድ ቀን ቦሌ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእሁድ አምልኮ ላይ መልእክት አቅርቤ በቮልስ ዋገን መኪናዬ ወደ ቤቴ በመመለስ ላይ ነበርኩ። በዚህ ጊዜ መኪና ውስጥ ብቻዬን ሆኜ መንገዱ ሳይቀር ጭር ብሎ ባለበት ጸጥታ የሰፈነበት ጊዜ ውስጥ ችርርር... የሚለውን የቮልስ ዋገኗን ሞተር ድምፅ አልፎ ልክ አጠገቤ ተቀምጦ ያለ ሰው የተናገረው የሚመስል "ወደ አሜሪካን ትሄዳለህ" የሚል ንግግር ሰማሁ።

ወዲያውኑም በአሜሪካን የሚያገለግለውና የቀድሞ የኔ ተማሪ የነበረው የፓስተር ሞገስ ቤተ ክርስቲያን እኔ ሄጄ እንዳገለግላት የጥሪ ደብዳቤ ጻፈችልኝ። ይህ ደብዳቤ ሲደርሰኝም አስቀድሜ የአገልግሎቴ ኃላፊዎች ለነበሩት ዶ/ር ተስፋዬ ያዕቆብ እና አቶ ኩርሴ ሽፈና አስገባሁ። አለቆችም ደብዳቤውን ከወሰዱ በኋላ እኔን ጠርተው "መሄድ ተፈቅዶልሃል ወይም አልተፈቀደልህም" ሳይሉኝ በቀጥታ ወደ አሜሪካን ጽፈው ደብዳቤ መሄድ እንደምችል ገለጹላቸው።

እኔም በጉዳዩ ላይ መጸለይ ጀመርኩ። በዚሁ ጊዜ የመሄዴ ነገር እንደ አንድ የቤተሰብ ኃላፊ ሲታይ ፈታኝ ነበር። እኔም በነገሩ ላይ ስጸልይ እግዚአብሔር "በእኔ እጅ ላይ ትተኃቸው ሂድ።" የሚል መልእክት ሰጠኝ። እኔም ይህንኑ ለባለቤቴ "እግዚአብሔር 'በኔ እጅ ላይ ትተህ ሂድ' ይለኛልና ምን ላድርግ?" አልኳት።

ባለቤቴ ወ/ሮ ታደለችም "አዎን በእግዚአብሔር እጅ ላይ ትተኸን ሂድ። ከዚህ በፊትስ ሄደህ አታውቅምና ነው?" አለችኝ። እኔም በዚህ ተበረታትቼ ለመሄድ ወሰንኩ። በመጨረሻም ሁሉም ነገር ተሳክቶ በ1994 ዓ.ም ሰኔ ወር ለሦስት ወራት ቆይታ ወደ አሜሪካ ሄጄ እስከ መስከረም አጋማሽ ቆየሁ።

በአሜሪካን ምድር እግዚአብሔር አስደናቂ የአገልግሎት ጊዜ ሰጠኝ። ከዚህ በፊት በሄድኩበት ጊዜ በአብዛኛው በነጮች ቤተ ክርስቲያን ያገለገልኩ ሲሆን በሄድንበት ስፍራ ሁሉ ጉዞውን የሚያስተባብሩ የቀድሞ ሚስዮናውያን አልተለዩንም ነበር። በዚህኛው ጉዞዬ ግን ወደ ተለያዩ ቦታዎች እየተጠራሁ አገለግል ስለነበር አሜሪካን ባሉ 12 ግዛቶች ስዞዋወር አውሮፕላን ውስጥ እና በአውሮፕላን ጣቢያዎች ውስጥ ለብቻዬ ነበር የተንገዝኩት። እግዚአብሔር ረድቶኝም በእነዚያ ሦስት ወራት ውስጥ 24 ጊዜ

በአውሮፐላን ስጓጓዝ አንድም ችግር ሳይፈጠርና ወደ ተሳሳተ ቦታ ሳልሄድ ወይም ተሳስቼ ጉዞ ሳይስተጓጎልብኝ ሰዓት እንኳን ተሳስቼ ሳላሳልፍ በስኬት ተጓጉዤ ማገልገል ቻልኩ።

በዚህ የአሜሪካን ጉዞዬ ወቅት ከቦታ ቦታ ስዘዋወር እኔ እንግሊዘኛ በደንብ ባልችልም በተወሰነ መስማት እችል ስለነበር ሰዎች እንድናገርም ሆነ እንዳደርግ ጽፈው የሰጡኝን አነብባለሁ። ከዚህ ሌላ ግን አብዛኛውን ጊዜ በምልክት እያሳየሁ እና በተሰባበረ እንግሊዘኛ እየተናገርኩ የምፈልገውን ሁሉ ማግኘት መቻሌ በጣም አስደናቂ የእግዚአብሔር ሥራ ነበር።

አሜሪካን እንደሄድኩ ተዘዋውሬ ሳስተምር ስለ ቅድስና በአጽንኦት እሰብክ ነበር። ይህንን በማድረጌም በየ ቤተ ክርስቲያኑ ያሉ አንዳንድ መጋብያን ከመጀመሪያው ቀን አገልግሎቴ በቀጣዩ ፕሮግራም ሰው ይቀራል ብለውን እንደሰጉ ይነግሩኝ ነበር። ነገር ግን የግሳጼ መልእክት እያቀረብኩ እንኳ ሕዝቡ ከመሸሽ ይልቅ ጭራሽ ተጠራርቶ በብዛት ይመጣ ነበር። ከአገልግሎቴ በኋላም መሪዎቹ "እኛ እንዲህ ያለ ስብከት ብንሰብክ ሰው ትቶን ይሄዳል ብለን እንሰጋለን።" ብለው እውነተኛ ስሜታቸውን ነገሩኝ። እኔም "እናንተ ይህን የምታደርጉት ሕዝቡ የገቢ ምንጫችሁ ስለሆነ ነው። ሰው ከቀረ ገቢ ይቀንሳል ብላችሁ ትፈራላችሁ። እናንተ የሕዝቡ ረዲዎች ሳትሆኑ ሕዝቡ ነው እናንተን የሚመራው። ይህን የምታደርጉት ለገቢው ስስታችሁ ነው።" አልኳቸው።

በዚህ ዓይነት በየቦታው እየዞርኩ እግዚአብሔር የሚሰጠኝን መልእክት ያቀረብኩ ሲሆን በየደረስኩበት ቦታ ሁሉ የሚያውቁኝና በፍቅር የሚቀበሉኝ ሰዎች አላጣሁም። እግዚአብሔርም በትክክል እየመራ ለየቦታው የሚሆን መልእክት እየሰጠኝ በድል አዞሮኛል።

በየሄድኩበት ቦታ ያገኙኝ ኢትዮጵያውያንም ትልቅ አክብሮት እና ፍቅር ያሳዩኝ የነበረ ሲሆን በየቦታው ሰዎች ልብስ እና ሌላም ስጦታ ሊገዙልኝ በተነሱ ቁጥር አሻፈረኝ እላቸው ነበር። ይህም ብዙዎቹን እያስገረማቸው "ሌሎች እርዱን ይላሉ፤ አንተ ደግሞ ፍላጎትህ የተለየ ነው።" ይሉኝ ነበር።

የአሜሪካን ምድር ከረገጥኩባት ጊዜ ጀምሮ በአስራ ሁለት ግዛቶች በዋሺንግተን ዲሲ ከተማ እና በዋሺንግተን ግዛት፤ በቨርጂኒያ፣ በአትላንታ፣ በካንሳስ፣ በኦሃዮ፣ እና ሌሎችም አካባቢዎች ለብቻዬ እየተዘዋወርኩ በኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያናት በጣም አስደሳች የአገልግሎት ጊዜ አሳለፍኩ። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች እንደ አንድ ልዩ ሰው በክብር እየተቀበሉ በሚያስፈልገኝ ሁሉ እያስተናገዱና የጎደለኝን ሁሉ እያሟሉ መልካም ጊዜ እንዳሳልፍ አደረገውኛል።

በየደረስኩበት በኢትዮጵያ የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት ያገለግሉ የነበሩ እና አባል የነበሩ አማኞች እኔን ሲያገኙ ሁሉም ልክ እንደ ዘመዳቸው በፍቅር ይቀበሉኝ ነበር። ብዙዎች ወደ እኔ እየመጡ "ጋሼ ኬዳሞ አንተ እኮ እንዲህ ብለህ መክረኸኝ ነበር" "... አንተ እኮ እንዲህ ተቆጥተኸኝ ይህን ማድረግ ችያለሁ። ... እንዲህ ብለህ የገሰጽከኝን ታስታውሳለህ ወይ?" እና ብዙ ብዙ እኔ የማላስታውሳቸውን በኢትዮጵያ የተፈጠሩ ገጠመኞች ይጠይቁኝ ነበር። እንደነ ሰናይት ኬዳሞ ያሉትም የአባታቸውን ስም ሁሉ ቀይረው አገኘኋቸው።

በእርግጥ የሰናይት ኬዳሞ ከሰው ሁሉ የተለየ ፍቅር ነው። አሜሪካ በመጀመሪያ የሄድኩ ጊዜ ካናዳ አግኝቻት ለእኔ እና አብሮኝ የነበረው አቶ መርከ.ና ሙሉ ልብስ፣ ጫማና ካልሲ ሳይቀር አሟልታ ገዝታልን ነበር። በአሁኑ ጉዞዬም እንዲሁ ብዙ ነገር አደረገች። ይኸው ጭራሽ ዛሬም በስም ብቻ ሳይሆን በተግባርም እንደ አባቷ ቆጥራ ለበዓል እና በተለያዩ አጋጣሚዎች ገንዘብ የምትልክልኝ እውነተኛ ልጄ ሆናለች።

በአሜሪካ ያገኘኋቸው ብዙ ጌታ የሰጠኝ ልጆቼም እኔ ሽክም ሳበዛ ባልፈልግም ሳላስበው እኔን ሳይጠይቁ ገዝተው እየመጡ በርካታ ስጦታዎችን አበርክተውልኛል። ያኔ ከአሜሪካን ተሰጥተውኝ ያመጣኋቸው አልባሳት ዛሬም ድረስ ሳያልቁ ለ11 ዓመታት ይህ አስፈለገኝ ብዬ ሳልገዛ እንድኖር አድርገውኛል። አንዳንዶች እኔ ለመቀበል አለመፈለጌን እያዩ ከነበራቸው አክብሮት እና ፍቅር የተነሳ በእምባ እና በመንቀጥቀጥ እያመጡ ነበር የሰጡኝ። እግዚአብሔር የአምስት አስርት ዓመታት አገልግሎቴን ቆጥሮ ሁሉን በታላቅ ፍቅር ከፈለኝ እንጂ እኔ ይህ ሁሉ የሚገባኝ አልነበርኩም።

አሜሪካን ያሉ ክርስቲያን ወገኖች በሚገርምና ባልጠበቅሁት ሁኔታ 50ኛ የአገልግሎት ዘመኔን የወርቅ ኢዮቤልዩ የመታሰቢያ በዓል አክብረውልኛል። ይህ ታላቅ በዓል የኔው ተማሪ የነበረውና ጌጃ አጥቢያ ውስጥ መልካም ጊዜን አብሮኝ ያሳለፈው ፓስተር ሞገስ ታደሰ በሚመራት ቤተ ክርስቲያን በድምቀት ለእኔ ልዩ የአገልግሎት መታሰቢያ በመስጠት የተከናወነ ነበር። ከልዩ ልዩ ቤተ ክርስቲያናት ከሙሉ ወንጌል፣ መሠረተ ክርስቶስ፣ ሕይወት ብርሃን እና ከሌሎችም የተገኙ ወገኖች በአንድነት በታላቅ አክብሮት ትልቅ በዓል አዘጋጅተው ደስ አሰኙተውኛል።

ከሁሉም የሚያስገርመው እኔ አሜሪካን በነበርኩበት ጊዜ በአገልግሎት 50 ዓመታትን እንዳሳለፍኩ ባውቅም በሰው አገር በእንግድነት በሄድኩበት ምድር ማንም አስታውሶ እግዚአብሔርን ስለማገልገሌ የተለየ ስጦታ እና ክብረ በዓል ያዘጋጃል ብዬ ግን አልጠብቅሁም ነበር። በበዓሉ ወቅትም ወደ አሜሪካ እንድሄድ ጋባዡ የነበሩት ሞገስ እና የሚያገለግለባት ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ የእኔን ቆይታ ሙሉ ኃላፊነት የወሰደው ሞገስ በበዓሉ ላይ ሳላውቀው የአገር ባህል ልብስ ለብሼ እንድገኝ እና እንድሰብክ አደረገ። ከዚያም እነርሱ አስቀድመው ባደረጉት ዝግጅት መሠረት ብዙዎች በተሳተፉበት ሁኔታ ደማቅ የአገልግሎት የወርቅ ኢዮቤልዩ ክብረ በዓል አደረጉልኝ። የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን።

አንድ ጊዜ አንድ ቦታ ሄጄ ሳገለግል በሄድኩበት ቦታ ለሰባት ቀናት ያህል ቆይቼ በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወርኩ አገለገልኳቸው። ከዚህ የአገልግሎት ቆይታ በኋላም ከነበርኩበት ወደ አሃዮ ነበር የምሄደው። ወደ አሃዮ በአውሮፕላን ለመሄድ ደግሞ በዚያ ጊዜ 600 ዶላር ያስከፍላል። እኔ ሳገለግል በቆየሁበት ቦታ ደግሞ እኔን ተቀብሎ ሊያስተናግደኝ የነበረው ካፒቴን ዮሐንስ የሚባል ወንድም ነበር። እርሱም በዚያ ስፍራ ሳገለግል ቆይቼ ለኔ ለመስጠት የተዘጋጀ 600 ዶላር ይዟል። የኔ አገልግሎት ማብቂያ ሲቃረብም ካፒቴን ዮሐንስ ሊሰጠኝ ስለተዘጋጀው ገንዘብ እና ስለ የጉዞ ወጪው ተጨንቆ አማከረኝ። "የተዘጋጀው ገንዘብ 600 ዶላር ነው። ወደ አሃዮ በአውሮፕላን ከሄድክ ደግሞ 600 ዶላር ትከፍላለህ። እናም ላንተ ምንም አይተርፍህም። ለምን በባቡር 200 ዶላር ከፍለህ አትሄድም?" ብሎ የጭንቀቱን ነገረኝ።

እርሱ ይህን ሲነግረኝም "እኔ ነጋዴ አይደለሁም። የገንዘብ ትርፍ አያስፈልገኝም። የኔ ትርፍ እግዚአብሔርን ማገልገል ነው። በዚያ ላይ የኔ ሰውነት የእግዚአብሔር ነው። እናም የእግዚአብሔርን ንብረት በባቡር ሙሉ ቀን ለ8 ሰዓት ያህል አስጉዤ ማሰቃየት የለብኝም። በአውሮፕላን እሄዳለሁ። አንተ አትጨነቅ።" አልኩት በባቡር ብሄድ አሃዮ ድረስ 8 ሰዓት ያህል ባቡር ውስጥ እንደምቀመጥ ነግሮኝ ነበር።

ይህንን ከተነጋገርን በኋላም ቤተ ክርስቲያናቸው ሄደን የመጨረሻውን መልእክቴን ከምስክርነት ጋር አድርጌ አቀረብሁ። በወቅቱ ያስተማርኩት በኤፌሶን መጽሐፍ ምዕራፍ 2፡1-10 ባለው ምንባብ ላይ ባለው ሃሳብ ነበር።

ይህ የቃሉ ክፍል ሙታን ነበራችሁ እንደሚል የኛም ዘር እንዴት ሙታን እንደነበርን፣ ዛፉን፣ አባብን እና ሌሎችን ሁሉ እናመልክ እንደነበር ነገርኳቸው። እናም ለፍርድ ተቀምጠን ከነበርንበት በኢየሱስ ደም እንደተዋጀን መሰከርኩላቸውና በጣም ተባረኩ።

በዚህ ጊዜ በዚያ ዕለት የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ አልነበረም። ነገር ግን ከመልዕክቱ በኋላ የመጋቢው ሚስት ተነስታ በእኚህ ሰው እንዲህ ተባርከን እኛስ የፍቅር ስጦታ በመስጠት ለምን አንባርካቸውም ብላ ገንዘብ ሊሰጡ፣ ሰበሰቡ። ይህንኑ ገንዘብም በመጨረሻ ሊሰጠኝ ወደ እኔ የመጣው ካፒቴን ዮሐንስ ስለነበር አስቀድመን የተነጋገርነውን አስቦ እየተደነቀ መጣ። በዕለቱ ተሰብስቦ የተሰጠኝ 1050 ዶላር ሲሆን አስቀድሞ በወሰንኩት መሠረት ለኔ የሚሆንም ብዙ ገንዘብ ይዤ 600 ዶላር ለአውሮፕላን ተከፍሎ ለመሄድ ችያለሁ።

ካፒቴን ዮሐንስም ተገርሞ "አንተ ገንዘብ አትወድም። ገንዘቡ ግን አንተን ይከተልሃል።" ብሎኝ ነበር። እኔም "እኔ እግዚአብሔር ለኔ ያዘዘው ይበቃኛል። በግሌም እስከ መቼ እንደምኖር በምን አውቄ ገንዘብ አጠራቅማለሁ? ስለዚህ ገንዘብ ለመያዝ አልጨነቅም። ይልቁንም የእግዚአብሔር መቅደስ የሆነው ሰውነቴ እንዳይራብ፣ መጥፎ ቦታ እንዳይተኛና እንዳይንሳቀል መጠበቅ አለብኝ።" አልኩት። እርሱም ይህ ለኔ ትልቅ ትምህርት ነው ብሎ እያለቀሰ ነበር የሰማኝ።

እኔም እግዚአብሔር ያደረገልኝንና የሰጠኝን ሞገስ ሳስብ ሁል ጊዜ ዓይኖቼ በእንባ ይሞላሉ። የሆነው ሁሉ በክርስቶስ በኩል በእርሱ ጥበብ እና እውቀት እርሱ በባዶው ዕቃ በሸክላ ውስጥ ገብቶ ከሠራው ሥራ የተነሳ ብቻ በመሆኑ እኔ ምንም ትምክህት የለኝም። እኔ እኮ ያንን ሁሉ ብዙ ሕዝብ፣ ብዙ ወዳጅ፣ ብዙ ወንድም እና እህት እንዲሁም ብዙ ልጆች ማግኘቴ ከጌታ የተነሳ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል "ስለ እኔ እናቱን፣ አባቱን ወንድሙን እህቱን ልጁን እና ሚስቱን እርሻውንም የተወ መቶ እጥፍ ያገኛል" ይላል። እኔ በሥጋ ከወላጆቼ ተወልደው የተዛመዱኝ ሦስት ወንድሞች እና አራት እህቶች ነበሩኝ፡፡ ነገር ግን ዛሬ ይኸው ጌታ በዓለም ዙሪያ የተበተኑ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ወንድሞች፣ እህቶች እና ልጆች ሰጠኝ።

በመጨረሻም ከአሜሪካን ወደ አገሬ ልመለስ ስነሳ በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለእኔ ስላደረጉት ቸርነት እንዲህ ስል ባረክሁአቸው። "ለእኔ ያላደረጋችሁት ነገር የለም። ያደረጋችሁት ሁሉ ደግሞ ከእግዚአብሔር የተነሳ ስለሆነ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን። ለእናንተም በረከት ይሁን" ብዬ ተሰናበትኳቸው። ወደ አሜሪካን እንድሄድ እና የነበረኝ ቆይታ ያማረ እንዲሆን በተለይም 50ኛ ዓመት የአገልግሎት ክብረ በዓል በማክበር፤ በመጨረሻም እራሱ ጋ አቆይቶ በክብር የሸኘኝን ሞገስ ታደሰን በጣም አመሰግነዋለሁ። በእውነትም ሞገስ ገና ጌጃ አጥቢያ እያለ ጌታን በጣም የሚወድድ እና እኔም አንድ ቀን የኔ ተተኪ ይሆናል ብዬ ሳስተምረው የነበረ ሲሆን አሜሪካንም ትልቅ አገልጋይ ሆኖ አይቼ እኔንም እንደ መንፈሳዊ አባቱ ተንከባክቦ መልሶኛልና እግዚአብሔር ይባርከው።

ወደ ኢትዮጵያ ልነሳ ዕቃዬን ሳዘጋጅም ጓዜ እጅግ በዝቶ ነበር። ፓስተር ሞገስ አራት ሻንጣ ገዝቶ አምጥቶ እዚያ ውስጥ ብንከት ... ብንከት ... ዕቃው ሊያልቅ አልቻለም። በመጨረሻም ዕቃውን በሻንጣ ከቶ መጨረሉ አቅቶኝ ጭንቅ ሲለኝ ትቼው አልጋ ላይ ወጣሁ እና ተኝቼ ማሰብ ጀመርኩ። ወዲያው መንፈስ ቅዱስ "አሁን እንዲህ ያስጨነቀህ መርገም የመሰለህ የዕቃ ብዛት እግዚአብሔር የሰጠህ በረከት ነው። ይህ ከእግዚአብሔር የተሰጠ በረከት ስለሆነ እንጂ ሌሎች ለምነው እንኳ አያገኙትም።" አለኝ። ወዲያው ከአልጋዬ ወረድኩ እና "እግዚአብሔር ሆይ ማረኝ፤ ይቅር በለኝ።" ብዬ ጭንቀቴን ከላዬ አራገፍኩ።

በኋላም የጉዞዬ ሰዓት ሲደርስ ዕቃዬን በአራት ሻንጣ አጭቀን ወደ አውሮፕላን ጣቢያ ሄድን። አብረውኝ ሊሸኙኝ ከሄዱት መካከልም ለአስተናባሪዎቹ ስለ እኔ ማንነት ተናገሩ እና እዚያ የነበረች አንዲት ክርስቲያን እህት ረዳችኝ። ወዲያውኑ እዚያው የኔን ዕቃ በሙሉ ዘክዝካ አወጣች እና በሦስት ሻንጣ ልክክ አድርጋ አስገብታ ቆለፈች። ከዚያም መዘነችው እና "75 ኪሎ ነው፤ አትከፍሉም" ብላ አሳለፈችኝ። እኔም ወደ አገሬ በደስታ በረርኩ።

ወደ አገሬ ስገባም አስቀድሜ ተጨንቄባቸው የነበሩ ሦስት ነገሮች ተሻሽለው ጠበቁኝ። በእርግጥ አሜሪካን ሆኜ ሁሌ ወደ ቤተሰቤ እየደወልኩ የባለቤቴን እና የልጆቼን ሁኔታ እጠይቅ ነበር። እግዚአብሔር ከቤተሰቤ ጋር ሆኖ ጠብቆኝም ባለቤቴም ጤናዋ በመጠኑ ተሻሽሎ፤ ልጄ ኃብተወልድም ተሽሎት፤ ትንሿ ልጄ ምህረትም በሰላም ተገላግላ የልጅ ልጄን ታቅፋ ጠበቀችኝ።

ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሕይወት መኖር እንዴት መታደል ነው!! መቼም ኪሳራ የለበትም። ስናገለግለው በአገልግሎቱ ሁሉ ከእኛ ጋር ሆኖ ያበጀናል፤ እየመራ ሞገስ ይሰጠናል፤ ከዚያም ምድራዊና መንፈሳዊም በረከት ይሰጠናል። ስሙ ይባረክ!!

---------------------------//---------------------------